# የግእዝ ቅኔያት

## የስነ ጥበብ ቅርስ

### ንባቡ ከነትርጓሜው

ከኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ
ባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር

www.ethiopianorthodox.org

መጽሀፉን በከፊልም ሆነ በሙሉ ለማሳተም መብቱ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ ነው ።

መጀመሪያ እትም 1980

አሳታሚ
የባህልና ስፖርት ጉዳይ ሚኒስቴር

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት
አዲስ አበባ

## የስራው ፕሮግራም ተሳታፊዎች

የአካዴሚው ጉባኤ የስነ ፅሁፍ ኮሚቴ አባላት ፤

አቶ ተክለ ፃድቅ መኩሪያ
ዶ/ር አምሳሉ አክሊሉ
ዶ/ር ሀይሉ አርአያ
አቶ መንግስቱ ለማ ( የኮሚቴው አስተባባሪ ) ።

የአካዴሚው ሰራተኞች ፤

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ
በምስጠራ ትረካና እረማ
አቶ ቀፀላ መንግስቱ ዳንኤል
በዝግጅትና ቅንብር
አቶ አእምሮ ፈረደ
በትርጎማ
አቶ መልክአ ክርስቶስ ነቢዩ
በግእዝና አማርኛ ታይፕ ስራ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ም ስ ጋ ና

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ጉባኤ የስነፅሁፍ ኮሚቴ አባላት በተለይም የኮሚቴው ሰብሰቢ አቶ መንግስቱ ለማ ለዚህ «የግእዝ ቅኔ የስነ ጥበብ ቅርስ » መፅሀፍ ዝግጅት ላበረከቱት ዘመናዊ የአሰራር ዘዴና የስራ ክትትል ፤

መፅሀፉን በማሳተም ረገድ ብርቱ ጥረት ላደረጉት ለአ ካዴሚው የቋንቋና የባህል ኤክስፐርት ለጓድ ዶክተር ኢሳይያስ አለሜና ለግእዝ ቅኔያትና መፃህፍት አንድምታ ትርጓሜ ክፍል ባልደረባ ለጓድ ቀፀላ መንግስቱ ዳንኤል ፤

በአካዳሚው ፅህፈት ቤት ስም አብዮታዊ ምስጋና አቀ ርባለሁ ፡

ከዚህም በቀር የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ሃላፊዎ ችና ሰራተኞች መፅሀፉ ጥራት ባለው መንገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ታትሞ እንዲወጣ ላሳዩት አብዮታዊ ትብብር ከልብ አመሰግናለሁ ፡

አሰፋ ገብረማርያም ተሰማ
የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ
ዋና ፀሀፊ

# ማ ው ጫ


| | | |
|---|---|---|
| መልእክት | ገፅ | 9 |
| መግቢያ | » | 11 |
| መቅድም<br>(የቅኔ ጥበብ አጀማመርና አረማመድ) | » | 15 |
| የግእዝ ቅኔያት ከነትርጓሜያቸው | » | 31 |
| የባለ ቅኔዎች አጭር ታሪክ | » | 433 |
| የባለ ቅኔዎቹ ስም ከቅኔዎቻቸው ተራ ቁጥር ጋር | » | 457 |
| የተዛማጅ መፃህፍት ዝርዝር | » | 463 |


www.ethiopianorthodox.org

# መልእክት

ኢትዮጵያ የረጅም ዘመን አኩሪ ታሪክ ያላትና የራሷ በሆነ ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህል የበለፀገች አገር መሆኗ የታወቀ ነው ። ብዙ ብሄረሰቦችን ያቀፈች አገር በመሆኗም የበርካታ ቋንቋዎችና ስነ ቃሎች ባለቤት ናት ። ከዚህም የተነሳ ኢሰፓና አብዮታዊው መንግስት ለሰፊው ህዝብ የባህል እንክብካቤ ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተውታል ።

ከታላቁ አብዮታችን መቀጣጠል ወዲህ በባህል ሚኒስቴር ስር በአዲስ ይዘትና ቅርፅ ከተቋቋሙት የምርምር ዘርፎች አንዱ የሆነው የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ የኢትዮጵያን ብሄረሰቦች ቋንቋዎችና ስነ ቃሎች በሳይንሳዊ መንገድ በመሰብሰብ ፣ በመመዝገብ ፣ በማጥናትና በመመርመር ላይ ይገኛል ።

አኩሪ ከሆነው የባህል ቅርሳችን አንዱ የግእዝ ቋንቋና ስነ ፅሁፍ በመሆኑ የአንድምታ ትርጓሜና የግእዝ ቅኔያትን ምርምር ስራ የሚያካሂድ በአካዴሚው ውስጥ ከተቋቋሙት የስራ ክፍሎች መካከል «የግእዝ ቅኔና መፃህፍት ትርጓሜ ክፍል» አንዱ ነው ። ክፍሉ የአካዴሚው ፅህፈት ቤትና የአካዴሚው ጉባኤ የስነ ፅህፍ ኮሚቴ በሚሰጡት መመሪያ መሰረት በርካታ ስራዎችን በማከናወን ላይ ሲሆን ፣ ይህ የመጀመሪያ የስራ ፍሬው የሆነው «የግእዝ ቅኔያት— የስነ ጥበብ ቅርስ» የተሰኘው መፅሀፍ ታትሞ መውጣት ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው ነው ።

ባህላዊው የግእዝ ቅኔ ለብዙ ምእት አመታት በግእዝ ቋንቋ ከመነገሩ ሌላ በፅሁፍ እምብዛም አይሰፍርም ነበር ። ከቅርብ ዘመን ጀምሮ ግን የግእዝ ቅኔያት ከታወቁ ሊቃውንት ተሰብስበው እንደታተሙና ለህዝብ እንደቀረቡ አይዘነጋም ። ረቂቅ የሆነው የግእዝ ቅኔ ስነ ፅሁፋዊ ጥበብ አሁን ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ምስጢሩ ተተንትኖና ተብራርቶ ለህትመት መብቃቱ አንድ አይነተኛ እርምጃ መሆኑ አይጠረጠርም ።

www.ethiopianorthodox.org

የግእዝ ቅኔያቱ ትርጓሜ በዚህ መልክና ቅርፅ ሲዘጋጅ ይህ የመጀመሪያው ጥራዝ ነው ። ተከታዩ እትም ወደፊት በቅርቡ ለአንባቢያን እንደሚደርስ በባህል ሚኒስቴር የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ ጉባኤ የስነ ፅሁፍ ኮሚቴ ሙሉ ተስፋ አለው ።

መንግስቱ ለማ

የአካዴሚው ጉባኤ ም/ ሊቀ መንበር



# መ ቅ ድ ም

## የቅኔ ጥበብ አጀማመርና አረማመድ

ከአለቃ አረመርቅ ዘውዴ የተዘጋጀ ።

በስድስተኛው ምእት አመት በአፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግስት የተነሳው ያሬድ በግእዝ መፃህፍት ምስጢር የተራቀቀ ሊቅ በመሆኑ ፤ ከመፃህፍት ጠቅሶ ከራሱም አንቅቶ አያሌ መዝሙራትን ከነዜማቸው ደርሷል ። እነዚህም መዝሙራት ፆመ ድጓ ፣ ምእራፍ፣ ድጓ ፣ በተባሉ መፃህፍት ሰፍረው ከትውልድ ወደትውልድ ሲተላለፉ እስካሁን ደርሰዋል ።

የያሬድ የመዝሙር ድርሰት በግጥም ረገድ አብዛኛውን ቤት አልባ ቢሆንም ፣ አልፎ አልፎ ቤት እየመታ ከስድ ንባብነት ወደ ጉትነት ያመራ ፣ በሰምና ወርቅ የተመሰጠረ ፣ በሁለትም በሶስትም አምስትም ቤት የተወሳ ሆነ ። ቢሆንም ሂደቱ የቅኔን መንገድ የተከተለ ነው።

ቤት አልባ ቅኔዎችና ቤተኛ ቅኔዎች ሁለቱም በያሬድ ድርሰት ውስጥ ይገኛሉ ። ለቤት አልባው ቅኔ ምሳሌ የሚከተለውን ጥቅስ ከድጓ ይመለከቷል ።

1 ውብዙኃን ኖሎት መጽኡ
ወሰእኑ ከሢቶታ ለእብን እምአፈ ዐዘቅት
እስከ ይመጽእ ያዕቆብ ።
ወከማሁመ መጽኡ ብዙኃን ነቢያት
ወሰእኑ ከሢቶታ ለጥምቀት
እስከ ይመጽእ ዐቢይ ኖላዊ

የዚህና የሚለጥቁት የግእዝ ጥቅሶች የአማርኛ ትርጉማቸው በዚ ፅሁፍ መጨረሻ በየተራ ቁጥራቸው ለብቻው ሰፍሯል ።

በቤተኛው የያሬድ ቅኔ ምሳሌ አሁንም ከፆመ ድጓ እንጠቅሳለን ።



www.ethiopianorthodox.org

እንግዶች ተማሪዎችን ኗሪዎቹ ተማሪዎች ተቀብለው ፤ በየ ጎጆአቸው አሳርፈው በሽሚያ እግራቸውን አጥበው ምግብ መግበው፣ በራሳቸው መኝታ አስተኝተው፣ሲያስተናግዷቸው ይሰነብቱና «ጓዴ»፣ «እይዋ» እያሉ በማናቸውም ነገር ያላምዷቸዋል ። እንግዶቹም ከለመዱ በሁዋላ የራሳቸውን ጎጆ ይሰራሉ ።

## የጥቅሶቹ ትርጓሜ ።

1 ብዙ እረኞች መጡና
ደንጊያይቱን ከውሃ ጉድጓድ
አፍ ማንሳት ተሳናቸው
ያእቆብ እስኪመጣ ድረስ ።
እንደርሱም (እንደዚሁም) ብዙ ነቢያት መጡና
ጥምቀት ማጥመቅ አልቻሉም
ታላቅ ጠባቂ (ክርስቶስ) እስኪመጣ ድረስ ።

2 የክርስቶስ አገር አዲስ ቤት
ፅድቅ/ እንግዳ የሚያድርባት ናት ፤
ፃድቃን (እውነተኞች) እርሷን ከወርቅ መረጡ ።

3 ከብልፅግና/ ፏፏቴ የንጉስን (የክርስቶስን) ጓር አጠጡ ፤
ከወንጌል/ ምንጭ እርሻውን አረኩ ።

4 በመለኮት ጨው አለምን አጣፈጡ
በሙሽራ ሚጉላ ቤት ሰላምን አርከፈከፉ ፤
ሀዋርያት የተረገመ ጠላትን
ከህዝብ አስወገዱ ።

5 በትድስናና በንፅህና አዳራሽ ስጋውን ገነባ
በሰረገላ ወደ ላይ መጠቀ
ከአለም የራቀ ክቡር ኤልያስ ።

6 ያልተዋረደ ያሬድ ተወረደ ፤
ለትኔዎቹ/ ልጆች ቤት አልሰራምና ።

www.ethiopianorthodox.org



7 በአስር አውታር መዝሙር እቀኛለሁ
የቸር ዘርአ ያእቆብ ገናናነቱን ፤ እንደ መምህር ያሬድ ።

8 ቃየል ስለሉድ በወንድሙ ላይ ቀንቶ በደለ ።
ሶምሶን ስውር የነገሩን ምስጢር ስውር በደሊላ ተጠመደ
እርሷ ከራሱ ጠጉር ጋር ሀይሉን ላጩች ።
ተነስቶ ከሴቶች የሸሸ ምስጉን ነው ፤
ንጉሳችን ዘርአ ያእቆብን ይረዳው ዘንድ ።

9 ከተሰበረ በሁዋላ ሰውነታችን/ ገንቦን አጠናው
ሸክለኛው/ ክርስቶስ በአዲስ ጥምቀት ውሀ ።

# የግዕዝ ቅኔያት ከነትርጓሜያቸው

## 1 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘአድማሱ (መልአከ ብርሃን)

ባሕቲቱ ነቢረ እግዚአብሔር ፈርሀ ፤
እምኢሀልዎ ንዋም እስመ ዓለመ አንቅሀ ።

ት ር ጉ ም

እግዚአብሄር ብቻውን መቀመጥን ፈራ ፤
ከአለመኖር/ እንቅልፍ አለምን አንቅቷልና (ቀስቅሷልና)

ም ስ ጢ ር

ብቻውን መቀመጥ የፈራ ሰው ጓደኛውን (አቀማማጩን) እንደሚሻ ሁሉ ፤ እግዚአብሄር ክብሩ በባህርዩ (ለብቻው ሆኖ) እንዳይቀር ሰውንና የሚኖርበትን አለም ፈጠረ ይላሉ ባለቅኔው።

## 2 ግእዝ ጉባኤ ቃና

መርቆሬዎስ አብ ይደልዎከ ፍሥሐ ፤
ሃይማኖት ወልድከ አምጣነ ለፈረሰ በጽሐ ።



www.ethiopianorthodox.org

### ታ ሪ ክ

ሆሳእና የተባለ ክርስቶስ ነው ። አህያዋንና ውርንጫዋን በማ ፈራረቅ ጋልቦ ከቢታንያ ኢየሩሳሌም ሲገባ ብዙዎች ህዝቦች ተቀበሉት ። ህፃናትና ሽማግሌዎች «በአርያም (በሰማይ) ያለህ መድ ሀኒት» እያሉ አመሰገኑት ። አይሁድ በቅናታቸው እንዳያመሰግኑት ህፃናትንና ሽማግሌዎችን ቢከለክሏቸው ድንጋዮች እንደሰው በመ ሙህ አምላክነቱን መሰከሩለት ። አይሁድ ግን በዚህ ቀንተው በመ ስቀል ላይ ሰቀሉት (ማቴ. 25 ፥ 9—17 ፤ 27 ፥ 1—66) ።

ዘካርያስ ከነቢያት አንዱ ነው ። የእግዚአብሄርን ነገር ሲሰ ብክ ፥ በቤተ መቅደስ መካከል ተገድሎ ደሙ በግፍ ፈሷል (ማቴ. 23 ፥ 29—39) ።

እስራኤል ከግብፅ ሲወጡ የሶፎር ልጅ ባላቅ ብዛታቸውን አውቆ በአገሩ እንዳይሄዱበት በተራጋሚ ሰው አስረግሞ ሊያጠፋ ቸው ወደደ ፤ ስለዚህ የመርገም ስጦታ ያለውን በለአም የተባለውን ሰው « ናና ረግመህ አጥፋልኝ» አለው ። እርሱም ከቤቱ ተነስቶ በአህያው ላይ ሆኖ ሲሄድ ግሩም የሆነ (የሚያስፈራ) መልአክ ታያ ትና ፈራችው ። ወደሁዋላ እያፈገፈገች ወደፊት አልሄድ አለች ። በዚህ ጊዜ በለአም ተናዶ ቢመታት «ከአንተ የበለጠ ግሩም መል አክ ቢታየኝ ነው ፥ ምን ትለኛለህ ? » በማለት በሰብአዊ ቃል ተና ገረችው ይባላል (ኢያ. 13 ፥ 22 ። ዘሁል. 22—24) ።

ሙሴ እስራኤልን እየመራ በሲና በረሃ ሲጓዝ ህዝቡ በውሃ ጥም ስለተጨነቁ ፥ ወደአምላኩ ፀልዮ ውሃ ከድንጋይ አፍልቆ አጠ ጥቷቸዋል ይባላል ።

## 43 አጭር ሆሳዕና

ማርያም ክርካዕ እንተ አሕመልመለት ቈጽለ
ጸገየት ድንጋሌ ወፈረየት ቃለ ።



www.ethiopianorthodox.org

### ት ር ጉ ም

ቅጠልን ያለመለመች ማርያም/ሎሚ
ድንግልናን አበበች ፥ ቃልንም አፈራች ።

### ም ስ ጢ ር

የለመለመች የሎሚ እንጨት ፍሬን እንደምታፈራ ከሴቶ ች መካከል የተመረጠች ቅድስት ማርያም ቃል የተባለ ኢየሱ ስን በድንግልና ፀንሳ ወለደች በማለት ባለቅኔው እምነታቸውን በቅኔ ያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

## 44 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ካህነ ደብረ ዘይት እብን ለባዌ መጽሐፍ ኵሉ ፤
አኮኑ ጸሐፈ ቅዳሴ እግዚእ በቃሉ ።

### ት ር ጉ ም

የደብረ ዘይት ካህን/ድንጋይ መፅሀፍን ሁሉ አስተዋይ ነው ፤
የጌታን ቅዳሴ በቃሉ ፅፎልና ።

### ም ስ ጢ ር

ቅዳሴውን በቃሉ አጥንቶ የሚፅፍ ካህን (ቁም ፀሀፊ) አስተ ዋይ ይባላል ፤ እንዲሁም ባለቅኔው የደብረ ዘይት ድንጋይ ክርስቶስን አመሰገነ ፥ እንደ ሰው ሆነ ይላሉ ።

## 45 ዕዝል ጉባኤ ቃና

መርዓተ ፃማ ታፈቅር ዘምስለ ስምዖን ተሀሉ ፤
እስመ ስምዖን አብ ፈጻሜ ግብረ ሰብእ ኵሉ ።

## እሰረ ንጉሰ

የጌታህን ፈለግ ትከተል ዘንድ የወዲያና የወዲህ ምስክር
ጊዮርጊስ !
በሁዋላችን የጮኸች ሴትን ታፈራርዳት ዘንድ ይገባል ፤
ዱርን የዞሩ የግፍና የበደል ወንዶች
በልጅዋ ላይ አይለዋልና (በርትተዋልና)፣
ዛሬም ሁሉ ተፈፀመ ።

## ም ስ ጢ ር

መልካም ጠባቂ ከበጎች ፊት ጠንክሮ አውሬውን ከተከላከለ ላቸው ፤ በጎቹ እንደማይበሉ ክርስቶስም መሞቱ አዳምንና ልጆቹን ከዲያብሎስ ቁራኛነት ነፃ ለማውጣት ነው ።

የበጎች እረኞች የነበሩ ሙሴና ዳዊት ግን በበጎች የተመሰሉ እስራኤልን ከበደላቸው የተነሳ አምላክ ሊያጠፋቸው ሲል፣ «እነር ሱን ከምታጠፋብን እኛን ጠባቂዎቻቸውን አጥፋን » ብለው አም ላክን ቢማለዱላቸውም እነርሱ እራሳቸው እስራኤልን ከማጥፋት አልተቆጠቡም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

የአሰረ ነጋሲው ምስጢር ደግሞ ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያ በገባበት ወቅት የሀገር ፀጥታ ስለተበላሸ ፣ ወንበዴዎች ሌሊት ደብ ድበውና አፍነው ልጅዋን የወሰዱባት አንዲት ሴት ስትጮህ የሚ ረዳት አጣች ። ስለዚህም ከዲማ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን መስከ (ከማርገጃው ቆማ) እየጮኸች አለቀሰች ። ይህንም ራሳቸው የቅኔው ባለቤት በማየታቸው ሰው የጨከነባት ያችን ሴት የዲማው ቅዱስ ጊዮርጊስ ፈጥኖ እንዲረዳት በቅኔያቸው (ሰማእቱን) ተማፅነዋል ።

## ታ ሪ ክ

ዳዊት የእስራኤልን ህዝብ አንድ ባንድ አስቆጥሮ የብዛታቸ ውን መዝገብ ከኢዮአብ ከተረከበ በሁዋላ በስራው ተፀፀተ ፤ እግዚአ ብሄርንም ይቅርታ ጠየቀው ። እግዚአብሄርም በነቢዩ በጋድ ቃል



ከሶስት መቅሰፍቶች አንዱን እንዲመርጥ አመለከተው ። እርሱም ይቅር ባይ እንደመሆኑ መጠን በሰው እጅ ከመውደቅ በእግዚአ ብሄር እጅ መውደቅን መረጠ ። ይኸውም ቸነፈር በስንዴ መከር ጊዜ ህዝቡን መግደል ጀመረ ፤ በመቅሰፍቱ ሰባ ሺህ ሰው ሞተ ።

ቀሳፊው መልአክም ኢየሩሳሌምን ሊያጠፋት ሲል ፣ እግዚ ብሄር ስለህዝቡ እልቂት አዘነ ፤ መልአኩን «ከእንግዲህ በቃህ እጅህን መልስ» አለው።ዳዊትም ቀሳፊውን መልአክ በኦርና አውድማ አጠገብ ባየው ጊዜ አምላኩን ለመነ ፤ በደሉንም ገልጦ «የበደልሁ እረኞቸው እኔ ስሆን ፣ እሊህ በጎች ምን አደረጉ ? በእኔና በአ ባቴ ቤት ላይ የቁጣህን እጅ ዘርጋ» አለ ። በዚህ ጊዜ ነቢዩ ጋድ መጥቶ መስዋእት እንዲሰዋ አዘዘውና እንዳዘዘው አደረገ ። መቅሰ ፍቱ ተግ አለ (2 ሳሙ. 24 ፣ 1—25) ።

ክርስቶስ ራሱን በቸር ጠባቂ፣ አማኞችን በበጎች ዲያብ ሎስን በአውሬ መስሎ ተናገሯል ። « ለዘመጽአ ኀቤየ ኢይሰድዶ ወኢያወፅኦ አፍአ (ወደእኔ የሚመጣውን አላባርረውም ፤ ወደውጭም አላወጣውም)» ባለው መሰረት በመጠበቁ ማጥፋት እንደሌለበት አረጋግጧል (ዮሀ. 10 ፣ 1—42) ።

በኢጣሊያ ወረራ ጊዜ በዲማ ጊዮርጊስ ደብር የሰው ግዙ የሆነች አንዲት ሴት ነበረች ። በበረሃ የሚኖሩ ሽፍቶች ሌሊት መጥተው የዚያችን አገልጋይ ሴት ልጅ ነጥቀዋት ሄዱ ። ቀኑ እሁድ ስለነበረ መወድስ ተቁሞ ሳለ ፣ በቅኔ ማህሌቱ ውስጥ መጥታ «ልጄን ወሰዱብኝ ወይኔ ! ወይኔ ! » እያለች ስታለቅስ አደረች ። ስለዚህ ነው ባለቅኔው «ሳዕለ ወለታ እስመ ኀየሉ» ያሉት ።

## 55 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ኢጸግበ ሰይፍ ዘዘካርያስ ወዓሊ ፤
ዘይሴሰዮ ዮሐንስ እስመ ውእቱ አቦሊ ።



www.ethiopianorthodox.org

## 96 መወድስ

ሰይፈ ኀይለ መንግሥት ቅንት መጠነ ምናቤ
ኀያል ዮሐንስ ውስተ ሐቌከ ሰላማ
በውቤ ሥንከ ወበላህይከ ለማ፤
ወትቤ ድንግል ቃለ አፉከ
እስመ ርእየ ለኢትዮጵያ አመቱ ሕማማ
ለለዕለቱ ዘያደክማ ፤
ወታዐብዮ ነፍስየ ለውቤ አምላከ ራማ ።
እምአሶርሂ ዘይፈጥር ዲበ ትእዛዝከ ጻማ
ሠራዊተ ቤትከ ተካፈሉ ሰቂማ ዲበ ሰቂማ ፤
ወእመ ተራከባ ንግሥ ወቤተ ክህነት እማ
ጽድቅ ወሰላም በመዋዕሊከ ተሳለማ ።

ት ር ጉ ም

ሀይለኛ (ብርቱ) ዮሀንስ ! በሰላማ / ወገብህ
በውቤ/ውበትህና በለማ/ ወዝህ የመንግስት ሀይል/ ሰይፍን
በምናሴ ልክ(እንደምናሴ) ታጠቅ ፤
የአፍህ ቃል/ ድንግልም በየቀኑ
የሚያደክማት የአገልጋዩ ኢትዮጵያ ህመምን
አየ እኮ አለች፤
የሰማይ አምላክ/ውቤንም ነፍሴ ታከብረዋለች አለች ።
በትእዛዝህ ላይ ድካምን በሚፈጥር አሶርም
የቤትህ ወታደሮች ምርኮን በምርኮ ላይ ተካፈሉ ፤
መንግስትና እናቷ/ ቤተ ክህነትም በተገናኙ ጊዜ
ሰላምና እውነት በዘመንህ ተዋደዱ(ተስማሙ) ።





ሰይፉን ከወገቡ የታጠቀ አርበኛ አለባበሱና የጦር መሳሪያ እያ ያዙ ከተፈጥሮ ውበቱ ላይ ተጨማሪ ውበት እንደሚሆንለት፤ አፄ ዮሀንስ በአቡነ ሰላማ ተቀብተው መንገሳቸውንና ውቤና ለማ በተ ባሉት አሽከሮቻቸው መታጀባቸውን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል። ደግሞ ቅድስት ማርያም መከራዋን ያራቀላት አምላኳን እንዳመሰ ገነችው ፣ የአፄ ዮሀንስ ትእዛዝም በየጊዜው የሚቃወሙትን የኢት ዮጵያን ጠላቶች ማጥፋቷንና ሰራዊታቸውም በምርኮ ላይ ምርኮ ማግኘቱን ባለቅኔው ተርከዋል ።

## 97 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ዘአድማሱ ( መልአከ ብርሃን )

እስራኤል ዕፀው አውፅእዎ እማኅበርሙ ልምላሜ
ለእንተ ደወየ ወይነ በለምጸ ከናፍር ጊሜ ።

ት ር ጉ ም

እንጨቶች / እስራኤል ከልምላሜ / ማህበራቸው
በከንፈሮች ለምጥ የታመመ ወይንን አወጡት ።

ምስጢር

እስራኤል በአራቱ ልማድ ለምጥ የያዘውን ሰው ከአንድነታቸው እንደሚለዩት ፣ ሌሎቹ እንጨቶች በክረምት ሲለመልሙ ወይን አለ መለምለሙን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

## 98 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ደብረ ከርም ይመስል ካህነ ብዙኀ ዕድሜ ፤
እስመ ዲበ ርእሱ ይጠውም ጸዐዳ ሐሚለተ ርእሰ ጊሜ ።



www.ethiopianorthodox.org

ሳር ለፈረስና ለበቅሎ ቢፈልጉ
ለኪሮስ ልብሱ ለማትያስም ምግቡ ሲሆን
የሊባኖስን ሳር በኤልያስ ዘመን አጡ ።

## ምስጢር

አንዱ ያገኘውን ሌላው ሲያገኘው ባለመቻሉ እያንዳንዱ ሰው የትለያየ እድል እንዳለው ቅኔው ያስረዳል። ይኸውም ሲታወቅ አንካሳ ሰው መንገድን በቀጥታ እንደማይሄድ ኤልያብ የታናሽ ወንድሙ የዳዊትን እድል አልታደለም ። ከዚህም ሌላ እሾሆች የበለስን ፍሬ እንደማያፈሩ የቆሬ ልጆችም የአሮንን እድል አልታደሉም ። አክ አብና አብድዩ ለፈረስና ለበቅሏቸው ያጡትን ሳር ማትያስ በላው ኪሮስም ተኛበት በማለት ባለቅኔው ስለሰው ልጅ ኑሮ ውጣ ውረድ ያላቸውን አስተያየት በቅኔያቸው አመስጥረዋል ።

## ታሪክ

ከእሴይ ልጆች ታላቁና ረገደ መልካሙ ኤልያብ ሲሆን ለመ ንግስት የተመረጠው ታናሹ ልጅ ዳዊት ነው ። ነቢዩ ሳሙኤል የፊቱን ግርማና የቁመቱን ታላቅነት በማየት ወደኤልያብ ሲመለ ከት እግዚአብሄር ወደዳዊት ተመለከተ (1 ሳሙ. 16 ፥ 1—13) ።

አሮን የሙሴ ወንድሙ ሲሆን ለክህነት ስራ ተመርጦ በደብ ተራ አሪት ሲያገለግል ኖሯል ። የቆሬ ልጆች ግን ያልተፈቀደላቸ ውን የአሮንን ስራ እንሰራለን በማለት ልብሰ ተክህና ለብሰው ሲያ ጥኑ ጢሱ ቢነካቸው ፥ ልብሰ ተክህኖው ሳይቃጠል ሰውነታቸውን የተለበለበ ግንድ አስመስሎታል (ዘሁል. 16 ፥ 1—35) ።

አክአብና አብድዩ ለፈረስና ለበቅሎ ለምለም ሳር ለመፈለግ ወንዝ ለወንዝ ሲሄዱ አብድዩ ነቢይ ኤልያስን አገኘው (1 ነገስ. 18 ፥ 3—16) ።



www.ethiopianorthodox.org

ዘማልቲ ጎይሉ (አባ)

በዘመነ ንጉሥ ብልጣሶር ለእሙ ሀለዉ
ገብረ መርዓዊ ወኢዮብ አርድእተ ንጉሢ ክርስቶስ
ወእመ ርእዩ አጽባዕተ በአረፍተ ቤት ይቡስ ፣
ዕፃ ንትፋሰስ እምተባሀሉ ፤
ወይርከባ ለዘይረከባ በዛቲ ለንግሥ ፣
ዛቲ እስመ አሐቲ
ወኢሀለውዋ ምንተ እምትንተ ሥጋ ወሥርወ ርእስ ።
ባሕቱ እምዐጸቦሙ አስተጻንዖታ ለነፍስ ፣
እስመ ለክልኤቱ ኢተውህቦሙ ጥበበ እደ ቶማስ ዲዲ
ሞስ ፤
ወእመ እንታክቲ አጽባዕት እንተ ትገሥሥ
በዓለ አጽባዕት እምቀደሞሙ በነሢአታ እምዓዕለ ፍሕስ ።

ት ር ጉ ም

የንጉስ ክርስቶስ ተማሪዎች ገብረ መርአዊና
ኢዮብ በንጉስ ብልጣሶር ዘመን ቢኖሩ
በደረቅ ቤት ግድግዳም ጣቶችን ቢያዩ ፣
እጣ እንጣጣል ይችንም በንግስ
የሚያገኛት ያግኛት በተባባሉ ነበር ፤
ይችው አንዲት ናትና ፣
የስጋ ጅማትና የራስ ስርም ምንም የሷትምና ።
ነገር ግን ነፍስን ማጥናት በጨነቃቸው ነበር ፤
ዲዲሞስ የተባለ የቶማስ እጅ ጥበብ ለሁለቱ አልተሰጣቸ
ውምና ፣
ያች ጣቱም የምትዳስስ ብትሆን ኖሮ
ባለ ጣት እሷን ከግንብ ላይ በመያዝ በቀደማቸው ነበር።

www.ethiopianorthodox.org

አድምፆ መቃብር ኢንከል ወረኪበ ሞት ወሰነ ጻዕር ፤
እስመ ኅጥአ ዘይቀትሎ አመ ተባጽሕዎ ፀር
ሳኦል ዘተውህቦ ሀብተ አክሊለ ወርቅ ወመንበር ።
ወአመ ተመከረ ኢዮብ በዕጸበ ደዌ መሪር
ተመነየ መቃብረ ወኢረከቦ ለመቃብር ።

ት ር ጉ ም

ከፈለጉት ሁሉ ይታጣል ፥
አንተስ ካልፈቀድህ የሚሰጠን ስራ ምንድን ነው ?
ከጉንዳን ትንሽ ቁራሽ እስከ ቀዝቃዛ የውሃ ጠብታ ድረስ ።
ይህስ ይቆየንና
በምድርና በሰማይ የምትኖር ጌታ ሆይ !
የምክር ምሰሶ (መወሰኛ) ከሆነ ምክርህ በቀር
መቃብርን ማግኘትን አንችልም ፥ የጭንቅ ወሰን የሆነ
  ሞትን ማግኘትም አንችልም ፤
ዙፋንና የወርቅ አክሊል ሀብት የተሰጠው ሳኦል
ጠላቶች በተገናኙት ጊዜ የሚገድለው አጥቷልና ።
ኢዮብም በመራራ ህማም ጭንቅ በተፈተነ ጊዜ
መቃብርን ተመኘና መቃብርን አላገኘውምና ።

ም ስ ጢ ር

የዚህ ቅኔ ምስጢር ማንኛውም ነገር መልካምም ቢሆን ክፉም ቢሆን ፥ ያለ እግዚአብሄር ፈቃድ እንደማይሆን ያመለክታል ። ይኸውም ሳኦልን ጠላቶቹ በድንገት በደረሱበት ጊዜ ጋሻ ጃግሬውን እባክህ ግደለኝ አለው ። ጋሻ ጃግሬውም ሳኦልን ሊገድለው አልፈለገም ፤ ስለዚህ ሳኦል በሎሌው እጅ መሞትን አላገኘም ። እንዲሁም ኢዮብ በቁስለ ስጋ እንገብግቦት (በቁስል በሽታ በመቃጠል) ከመ ሰቃየት ይልቅ ሞትን ቢመኝ አልሆነለትም በማለት ሰው የፈለገውን በጊዜው ሊያገኝ እንደማይችል ባለቅኔው አረጋግጠዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

## 200 መወድስ

ዘከብቱ (ዐቃቤ ሰዓት)

እፎ ንሬኢ ገጸ ሆሣዕና
እለ በከንቱ ፈጸምነ ነሶሳወ ክልኤ አእጋር ?
እስመ ጸድቀተነ ንኅብ በጣዕመ ዚአሃ መዓር ።
ወኢነባብያን ምሳሌያት
ለገሥጾትነ ተንሥኡ እምድር ፤
እምጣነ ለከንቱ ኢትትባደር
ሐዋርያዊት ዕፅ ማኅደረ ብእሲ በሊሐ ምክር ።
ወይግበር ከመ ገብርዎ ሞሠርተ ሐፂን ግቡር
በሑረት ወበግብአት እንበለ ረባሕ ኢየሐውር ፤
ወየዋህ ለርእሱ ጠቢብ በወርኀ ማእረር
አቅድሞተ ዘርዕ እንዘ አልቦቱ ምስለ እለ ዘርዑ የአርር ።

ት ር ጉ ም

የሁለት እግሮች ምልልስን በከንቱ የፈፀምን እኛ
የሆሳእናን ፊት እንዴት እናያለን ?
ንብ በማሯ ጥፍጥና በልጣናለችና ።
የማይናገሩ ምሳሌዎችም
እኛን ለመገሰፅ ከምድር ተነሱ ፤
የምክረ ፈጣን ሰው
ማደሪያ የሆነች የሸማኔ መወርወሪያ ለከንቱ
  አትቀዳደምምና ።
የተሰራ የብረት መጋዝም እንዳደረጉት ያደርግ ዘንድ
በመሄድና በመመለስ ያለጥቅም አይሄድምና ፤
ለራሱ ጥበበኛ ገር ሰውም በአዝመራ ወራት
ዘር ማስቀደም ሳይኖርበት ከዘሩት ጋር ይለቅማልና ።

በዓለ ፈረስ ረኃብ ወደዌ ቀሊለ እግር ፣
ለረኃብ ይቀድሞ ጊዜ ምህርካ ሰብአ በግብር
ደዌ ውስተ ዓለም በክነፈ ነፋስ ዘይሰርር ፤
ወከመ ዕራቃ ኢትኩን ገራህተ ዓለም መንበር
አንግሥ ምሕረተከ አምላከ ሙሴ ወአልዓዛር ።

## ት ር ጉ ም

ከበቀል ንፁሃን እንሁን ፤ ከተሰራ
የህማም መስዋእት/ ሰው ለነገ አያድርምና ፤
መብል በአፉ ውስጥ ሳለ ወደ መራራ ሞት
የፍጡር ሁሉ መጠራትም እንደ አጋግ ሆኗልና ።
ባለፈረስ/ ራብና
በሽታ/ እግረ ቀላል ሁለታቸው ሲሮጡም ፣
ወደአለም በነፋስ/ ክንፍ የሚበር በሽታ
በሰው ምርኮ ጊዜ በግድ ራብን ይቀድመዋል ፤
የአለም እርሻ/ ወንበርም ባዶዋን እንዳትሆን
የሙሴና የአልዛር አምላክ! ይቅርታህን አንግስ ።

## ም ስ ጢ ር

የቁርባን መስዋእት ለነገ እንደማያድር እያንዳንዱ ህመምተኛ በአንድ ቀን የሚሞት ሆነ ። አጋግንም ነቢይ ሳሙኤል በጦር ሲወጋው ሞቱ መራራ እንደሆነ የህመምተኛው ውጋት አሰቃቂ ሆነ ። ወደንጉስ በአስቸኳይ የተጠራ ሹምም የጎረሰውን ሳይውጠው እንደ ሚሮጥ መቅሰፍቱ አጣዳፊ ነው ። ባለፈረስና ባለሰረገላም ሲሮጡ ባለፈረሱን ባለሰረገላው (ባለመኪናው) እንደሚቀድመው የነፋስ በሽታ ከራቡ በፊት ሆነ ። አለምም ባዶዋን እንዳትቀርና እርሻ መንበርም (ዙፋን) ጠፍ እንዳታድር ዘር መንግስት ,እንደሚዘራባት አምላክ ሆይ ! ይቅርታህን አድርግልን በማለት ባለቅኔው የነፋስ በሽታና የክፉ ቀንን አሰቃቂ ገፅታ በቅኔያቸው ተርከዋል ።





እግዚአብሔር አንተን በመበደል ጊዜ
የሚያህለኝ የለም እኔን ከፈጠርኸው ሁሉ ፍጡር ፤
እመስላለሁና መቼም ይሁዳ ወንድሜን በግብር
ምንም ብበልጠው በጥበብ በነውር
ካባቴ ከነዌ ጋር
የተካከልሁ ነኝ እኔም ወርቅና ብርን በማፍቀር ።
እንብላ እንብላ ሲሉ ሰዎች ስጋ መልከኛው ቢቀር
ቆርጠው የሄዱ ብዙ ናቸው እኔን ጨልሞኝ ስድበረበር ፤
ከነጋም ወዲያ እንዳልሄድ እሊያ በሄዱበት አገር
ይጠብቀኛል ከሁዋላዬ የሁሉ ጠላት መቃብር ።

## ት ር ጉ ም

ይህ ቅኔ በአማርኛ ቋንቋ የተደረሰ ስለሆነ መተርጎም አላስፈለገም ። ስለዚህ የሰምና ወርቁ ምስጢር ብቻ እንደሚከተለው ይነገራል።

## ም ስ ጢ ር

አንዳንድ ብልጥ የግለሰብ ተቀጣሪ «ጌታዬ ሆይ ! የእኔን ያህል ያገለገለ አሽከር የለህም ። ግን ያገልግሎቴን ዋጋ አላገኘሁም» በማለት ለቀጣሪው አገልግሎቱን ይዘረዝራል ። እንዲሁም አንድ ተነሳሂ (ተፀፃች) ባለቅኔ እግዚአብሄርን በመለማመጥ ፣ የራሳቸውን ሀጢአት ከፍ የሌላውን ሀጢአት ዝቅ በማድረግ ተቀኝተዋል ። ራሳቸውንም ከይሁዳ ጋር አነፃፅረዋል ። ምክንያቱም ይሁዳ የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ሲሆን ክርስቶስን ለገንዘብ ብሎ እንዳሰቀለው ሁሉ ፣ የክርስቶስን ህግ በገንዘብ ፍቅር ማፍረስ በባለቅኔው እምነት ክርስቶስን እንደመስቀል ስለሆነ ነው ። ሀብታምንም ሀብታም እንደሚወዳደረው ገንዘብን በመውደድ ባለቅኔው ለድሀ አልአዛር ያልራራ ነዌን እንደሚወዳደሩ አረጋግጠዋል።

www.ethiopianorthodox.org

### ምስጢር

በረዶ ሲባል ሁሉም በፀሀይ ሙቀት ስለሚሟሟና ሙብረቅ ሲባል ሁሉም አየር ወለድ ስለሆነና አንዱ ካንዱ የሚበልጥበት ምክንያት ስለሌለው ሰውም ሲባል ሁሉም አላፊና ጠፊ ስለሆነ ፣ እያንዳንዱ ሰው ሰርቶ ማግኘት እንጂ ከሁሉ በላይ የሆነ አምላክ እያለ አንዱ ላንዱ የገንዘብ ተገዥ ሙሆን የለበትም ። ምክንያቱም አለም ጥዋት ታይታ ማታ እንደምትረግፍ አበባ ናትና በማለት የቅኔ አባት ተዋነይ አመስጥሯል ።

## 207 ዕዝል ዕጣነ ሞገር

ፀሐየ ሰማይ ያውዒ ሀገረ መርቁ ርኁቅ
እንዘ ቅርብቶ ደደከ ኢያመውቅ ፤
ዝኒ ሕንጻ ምሳሌ ፀሐየ አሞንዮስ ሊቅ
ከመ ኢያንቀልቅል በጥዩቅ ፤
ለዐይነ ሄሮድስ ቅሩብ እንዘ ውእቱ ረቂቅ
ለዘርኀቁ ነገሥተ ጽባሕ ተግህደ በጽድቅ ።

### ትርጉም

የሰማይ ፀሀይ ፣ የቀረበችው ደጋን ሳያሞቅ
ሩቅ የቆላ አገርን ያሞቃል ፤
ይህም የምሳሌ ህንፃ ለሊቅ አሞንዮስ ፀሀይ
በተረዳ ነገር እንዳይናወጥ ፤
ለቅርብ ሄሮድስ አይን ረቂቅ ሲሆን
ለራቁ የምስራቅ ነገስታት በእውነት ተገለጠ ።

### ምስጢር

ፀሀይ አቅራቢያውን ደጋን (ተራራ ኮረብታውን) ሳያሞቅ የራቀውን በረሃ እንደሚያግለው ሁሉ ፣ ፀሀይ የተባለው የአሞንዮስ ጌታ ክርስቶስም በአቅራቢያው ላለው ለሄሮድስ ሳይገኝለት ከሩቅ አገር ለመጡት ለሰብአ ሰገል መታየቱን ባለቅኔው ያስገነዝባሉ ።



### ታሪክ

ኢየሱስ በቤተ ልሄም ከድንግል ማርያም በተወለደ ጊዜ የጥበብ ሰዎች ሶስት ነገስታት ከምስራቅ አገር መጡና በከብት በረት ለተወለደው ህፃን ሰገዱለት ። ወርቅና ከርቤ እጣን ገበሩለትና በሌላ መንገድ ወደአገራቸው ተመለሱ ። የገሊላ ንጉስ ሄሮድስ ግን በቤተ ልሄም የተወለደውን ህፃን ክርስቶስን ሊያገኘው አልቻለም (ማቴ. 2) ።

## 208 ዕዝል ጉባኤ ቃና

ዘገብረ መድኅን (አለቃ ፣ ዘአሰቦት)

እነግር አነ ለገብረ ሚካኤል ጽድቆ ፤
እስመ ገብረ መድኅን አነ ወመኑ ይከልአኒ ተጠምቆ ፤

### ትርጉም

እኔ የገብረ ሚካኤልን እውነቱን እናገራለሁ ፤
እኔ ገብረ መድህን ነኝና ፣ መጠመቅንስ ማን ይከለክለኛል።

### ምስጢር

በመጠመቅ (ክርስትና ሲነሱ) ገብረ መድህን መባል ስርአት እንደመሆኑ ፣ ገብረ መድህን የተባሉት መምህር ተጠምቆ ከተባሉ መምህር ጋር በሙያ አንድ መሆናቸውን በቅኔያቸው ምስጢር ያስገነዝባሉ ።

### ታሪክ

አለቃ ገብረ መድህን ፣ አለቃ ገብረ ሚካኤልና መምህር ተጠምቆ የትምህርት ቤትም የሙያም ጓደኞች ናቸው ። ከእለታት በአንዱ ቀን ሶስቱም አብረው ምስጢራዊ ጨዋታን ሲጨዋወቱ አለቃ ገብረ መድህን ስለሁለቱ ጓዶቻቸው ይህን ቅኔ ዘረፉ ይባላል ።



www.ethiopianorthodox.org

## 209 ሥላሴ

ዓለመ ሥጋነ
ዐባይ ባሕር ዘርኢክዋ
ድምርት ይእቲ በእሳተ ብዙኅ ተጽዕቆ ፤
ወእለ ውስቴታ ዘነሥኡ መሰንቆ ።
ወለብእሲሃ ጥበብ ዘወይነ መንሱት አውደቆ
አልቦ ረድኤት ዘይሰውቆ ፤
ወእኅቱ ፍጽምት ደማስቆ
ታስቆቅዎ ሐቂፋ ደቂቆ ።

### ት ር ጉ ም

ያየሁዋት ትልቅ
ባህር / የስጋችን አለም
በብዙ መጨነቅ እሳት የተዶለች ናት ፤
በውስጧ ያሉትም መሰንቆ እንደያዙ የተሞሉ ናቸው።
ጥፋት /የወይን ጠጅ የጣለው ጥበብ/ ባሏንም
የሚደግፈው ረዳት የለም ፤
ፍፁም እህቱ ደማስቆም
ልጆቹን አቅፋ ታለቅስለታለች ።

### ም ስ ጢ ር

ሀዋርያው ዮሀንስ በራእዩ «ከእሳት ጋር የተቀየጠች ባህርን አየሁ» ባለው አንፃር የእሳት ባህር ምሳሌ የሆነችው ይህች የስጋችን አለም በጭንቀት የሚኖርባት ናት ። የሚኖሩባትም ሰዎች አነሰኝ ላብዛው ጠበበኝ ላስፋው በማለት አሳብ የተዋጡ ናቸው ። ደግሞ በወይን ጠጅ የሰከረ ሰው ባልሆነ ቦታ ሲወድቅ ፤ የሚያነሳው እንደማያገኝ የአለምም ጥበብ ከጥፋት አያድንም ። ከዚህም ሌላ



ለሞተ ሰው እህቱ ልጆቹን አቅፋ እንደምታለቅስለት የአለምና የወዳጇ ምሳሌ በእሳት የተቃጠለችው ደማስቆ መሆኗን ባለቅኔው አስረድተዋል ።

## 210 መወድስ

አትሮንስ ረኃብ ሰሎሞን ድንግለ ኢያሱ
አቤሜሌክ ግፍዕ ኤርምያስ ዘአልሀቆ
አዕረገ ብኪ እግረ ተሣልቆ ፤
ለገጽኪ ፈሪሳዊ
ዮሐንስ ተሰዶ አኮኑ አጥመቆ ።
ወተመሥጠ ልቡናኪ
በዘልቡና ይመሥጥ ድምፀ ሰቆቃው መሰንቆ ።
ረኃብሂ አምላኮሙ ለሰብአ ብዙኅ ናፍቆ
ለቃዴስ ልቡናኪ በግብጽ ያድለቀልቆ ፤
ወእንዘ ይዘርዕ ነግሀ ዘርዐ ልቡና ተጽዕቆ
ለእብን መልዕልቴሃ ቦ ዘይወድቆ ።

### ት ር ጉ ም

የሰሎሞን / ራብ ዙፋን / የኢያሱ ድንግል !
ኤርምያስ ያሳደገው አቤሜሌክ / ግፍ
ዝብብት / እግርን አወጣብሽ ፤
የፋሬስ ወገን / ፊትሽን
ዮሀንስ / መሰደድ አጥምቆታልና ፤
ልብን በሚመስጥ
በልቅሶ / መሰንቆ ድምፅም ልብሽ ተመስጧልና ።
የብዙ ጥርጥር ሰዎች አምላክ / ራብም
በረሃ / ልብሽን በግብፅ ያናውጠዋል ፤
የልብ ዘር / መጨነቅንም በጠዋት ሲዘራ
በድንጋይ ላይ የወደቀ ዘር አለ ።

www.ethiopianorthodox.org

### ም ስ ጢ ር

ቤተ ሰሪ አረግ እንደሚመዝ የአዳምና የሄዋን በለስን መብላት ሰማያዊው እግዚአብሄር ወልድን ሰው ለመሆን አደረሰው ። ደግሞ አንድ ጓድ ጓደኛውን በእጁ እንደሚጠቅሰው ፣ የአዳምና የሄዋን በለስን መብላት ገብርኤል የተባለውን መልአክ የወልድን መፀነስና መወለድ ለቅድስት ማርያም እንዲያበስር አደረገው ።

ከዚህም ሌላ መጠጥ ሲደጋግሙት እንደሚያረካ በለስን ቆርጠ መብላት ወልድን የስጋ ዘመዳችን ካደረገልን ፣ አዳምና ሄዋን ዳግመኛ በለስን ቆርጠው ቢበሉት አብም እንደ ወልድ በስጋ ይዘመደን ነበር ይላሉ ባለቅኔው ።

## 213 ሥላሴ

ወልድ ፈደለ ዐርብ
ላዕሌሁ ለዕፅ አመ ተሰፍሐ
ሕማማተ ሥጋ ደቂቅ ከመ ኪያሁ ያንብቡ
ሣዕረ ቀኖተ ሐፂን ነሢአሙ ቀርቡ ፤
ለመምህሮሙ ትጉህ ይሁዳ እንተ ፈድፈደ ጥበቡ
ሠላሳ ብሩር አምጣነ አሰቡ ።
ወጽሕፈተ ዝንቱ ፈደል በማይ ኀፀቡ ፤
እስመ ሖረ ውስተ ደይን ምስካቡ ።

### ት ር ጉ ም

የአርብ ፊደል/ ወልድ
በእንጨት ላይ በተዘረጋ ጊዜ
የስጋ ህማሞች / ልጆች እርሱን ያነቡ ዘንድ
የብረት ችንካር / ሳርን ይዘው ቀረቡ ፤
ጥበቡ የበዛ የትጉ መምህራቸው ይሁዳ



www.ethiopianorthodox.org

ደመወዙ ሰላሳ ብር ነውና ።
የዚህንም ፊደል ፅህፈት በውሃ አጠቡ ፤
ወደ ቅጣት / መኝታው ሄዷልና ።

### ም ስ ጢ ር

የህፃናት መማሪያ ፊደል በእንጨት ላይ ተዘርግቶ ልጆች በሳር እየነኩ እንደሚቆጥሩት ፤ ወልድ አርብ ቀን በእንጨት መስቀል ላይ ተሰቀለ ፣ በችንካር ተቸነከረ ፣ የስጋ መከራንም ተቀበለ ። የልጆቹም መምህር በሰላሳ ብር እንደሚቀጠር ይሁዳ ወልድን ለሰላሳ ብር ሸጠው ። መምህሩ ከክፍሉ ሲወጣ ትንንሾቹ ልጆች ፊደሉን በውሃ እንደሚያጥቡት ከወልድ ጎንም ውሃ ፈሰሰ ። ይሁዳም ወደቅጣት ቦታ ወረደ በማለት ባለቅኔው ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

## 214 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ረቢ ሰገደ በመንፈቀ ሌሊት ለረቢ ፤
አኮኑ አጽባዕት እምነ አጽባዕት የዐቢ ።

### ት ር ጉ ም

መምህር በእኩለ ሌሊት ለመምህር ሰገደ ፤
ከጣት ጣት ይበልጣልና ።

### ም ስ ጢ ር

ከጣት ጣት እንደሚበልጥ ፣ ከመምህር መምህር ስለሚበልጥ ከላቀው መምህር ዝቅተኛው መምህር ጠይቆ ይረዳል ። እንዲሁም የአይሁድ አለቃ ኒቆዲሞስ በኢየሱስ አምኖ ፣ አምላክነቱን መስክሮ ሌሊት ለኢየሱስ መስገዱን የቅኔው ምስጢር ያስረዳል ።

ባሀታዊ ! የሁለቱ አይኖች ምስጢርን አትግለጥ ፣
ቀላል ወፍ በከንቱ ያወጣዋልና ።

### ም ስ ጢ ር

ለቀላል ሰው ምስጢር ቢነግሩት ለማንም እንደሚያወጣው ፣ የገብረ መንፈስ ቅዱስን አይን የዱር ወፍ አወጣው ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

## 228 ዋዜማ

ለሥጋ ድንግል ደኃራዊ
መኑ ይነግር በይነ ሰማያዊ ልደቱ ?
እምድር እስመ ተአተተ መቃብር ሕይወቱ ።
በልማደ ሲኦል ይብል ዕፄ መቃብር ባሕቱ
ተውህቦ ሥጋ ለሀጕል ይምሥጠኒ ዝንቱ
ሰማያዊ ደመና በከንቱ ።

### ት ር ጉ ም

ለሁዋለኛው የድንግል ስጋ
ስለሰማያዊ ልደቱ ማን ያወራል ?
ህይወቱ መቃብር ከምድር ተወግዷልና ።
ነገር ግን በሲኦል ልማድ የመቃብር ትል
እርሱ የሰማይ ደመና በከንቱ ለጥፋት ይነጥቀኝ ዘንድ
ስጋ ተሰጠው ይላል ።

### ም ስ ጢ ር

ለወልድ የማይመረመር ሰማያዊ ልደት እንዳለው የድንግል ማርያም ስጋ ከመቃብር ተነስቶ ወደሰማይ መውጣቱን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ።



እንዲሁም ዲያብሎስ ነፍሳትን እንደተነጠቀ የመቃብር ትልም የማርያምን ስጋ በደመና አጣ በማለት ባለቅኔው የቅድስት ማርያ ምን ስጋ በመቃብር መፍረስና መበስበስ ያላገኙት መሆኑን በቅኔ ያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

## 229 ዋዜማ

ዘማህሌ ወልደ ተክሌ

እምአብርሃም መጋቤ ሕግ
ሲሳየ ዕለት ኀሠሡ እጋዕዝተ ሙሴ ሠለስቱ ፤
ኅዳጥ ሲሳየ ዕለት እስመ ፈውስ ውእቱ ።
ውስተ ቤተ ሙሴሰ ኪራም ዘኢየኀልቅ ንብረቱ
ኢኀሠሡ መና ብዙኀ ከመ ኢይሙቱ ፤
አበዊነ እስመ ኀልቁ ቦቱ ።

### ት ር ጉ ም

ከህግ መጋቢ /አብርሃም
ሶስቱ የሙሴ ጌቶች የእለት ምግብን ፈለጉ ፤
ጥቂት የእለት ምግብ መድሃኒት ነውና ።
ንብረቱ በማያልቅ በሙሴ / ኪራም ቤት ውስጥ ግን
እንዳይሞቱ ብዙ መናን አልፈለጉም ፤
አባቶቻችን አልቀውበታልና ።

### ም ስ ጢ ር

መንገደኞች ካለው ሰው ቤት የእለት ምግብን ፈልገው በራብ ከመሞት እንደሚድኑ ስላሴም በአብርሃም ቤት በሉ ። ከዚህም ሌላ መንገደኞች በሚጠረጥሩት ሰው ቤት ምንም ነገር እንደማይቀምሱ ፣ ስላሴም ከሙሴ መና አለመቅመሳቸው እስራኤል ስለሞቱበት ነው ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።

www.ethiopianorthodox.org

### ታ ሪ ክ

ስላሴ በአብርሃም ቤት ገብተው በእንግዶች አምሳል የቀረበላቸውን ተቀብለዋል ። እስራኤል አርባ ዘመን ሲጓዙ መና ከሰማይ እየወረደላቸው ተመግበዋል ፤ ከእነርሱም ብዙዎቹ እየታመሙ እንደቅጠል ረግፈው እንደሻሸ ተነጥፈው በዱር ቀርተዋል ይባላል። (ዘፍጥ.18 ። ዘፀአ. 16 ፥ 13—36 ) ።

## 230 ዋዜማ

ፈሪሳውያን ወብእሲት
ምክንያተ ዕልው ሄሮድስ ወሄሮድያዳ ክልኤቱ ፤
ብዙኃን እስመ በአሐቲ ዘመዉ እምጥንቱ ።
እመሰ ይትረከብ ሠራዔ ሕግጋት እሉንቱ
ሰብዑ አንስት እምኮና ለሰብዐቱ ፤
ወአሐቲ ለዋሕድ ዝንቱ ።

### ት ር ጉ ም

ፈሪሳውያንና ሴት
የሁለቱ የወንጀለኛው ሄሮድስና የሄሮድያዳ ምክንያት
ናቸው ፤
ብዙዎች ባንዲቱ ከመጀመርያ በድለዋልና
እነኝህን ህጎች ሰሪ ቢገኝ ግን
ሰባቱ ሴቶች ለሰባቱ ወንዶች በሆኑ ነበር ፤
አንዲቱም ለዚህ ለአንዱ በሆነች ነበር ።

### ም ስ ጢ ር

ባለቅኔው የፈሪሳውያንና ያንዲት ዝሙት አዳሪ ሴት ስራ ከሄሮድስና ከሄሮድያዳ ስራ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን በቅኔያቸው ገልጠዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

## 231 ዋዜማ

ዘገብረ ሚካኤል ዕሙር ( ዘሰላሌ )

ነጸረ ሰማዕተ ልዳ
ተቅዋመ ሥቃይ ዘመነ ዘአዕጹቂሃ ሰብዐቱ
እንዘ በውስቴታ ነበልባል የኀቱ ።
ወኁልቈ ሰብዐቱ አክራም ዘወሰኖሙ ዕረፍቱ
በኀበ ዕብራዊ መጥባሕት ፍጹም ውእቱ ፤
ወዐሥር በኀቤነ ሞቱ ።

### ት ር ጉ ም

የልዳ ሰማእት (ጊዮርጊስ)
ጫፎቿ ሰባት የሆኑ የስቃይ መቅረዝ ዘመንን አየ ፤
በውስጧ ነበልባሉ ሲበራ ።
እረፍቱ (ሞቱ) የወሰናቸው የሰባቱ ዘመኖች ቁጥርም
በእብራዊ ሰይፍ ዘንድ ፍፁም ነው ፤
አስርም በእኛ ዘንድ ሞቱ ነው ።

### ም ስ ጢ ር

ዘካርያስ ጫፎቿ ሰባት በሆኑ መቅረዞች ላይ ሰባት መብራት ሲበራ እንዳየ ፤ የልዳ ሰማእት ቅዱስ ጊዮርጊስም ሰባት አመት በእሳት መሰቃየቱን ቅኔው ያስረዳል ።

ደግሞ በኢትዮጵያውያን ዘንድ አስር ቁጥር፣ ሰባት ቁጥርም በእብራውያን ዘንድ ፍፁም (መጨረሻ ፡ሙሉ) እንደሆነ፣ የጊዮርጊስ የሰባት አመት ስቃይ መጨረሻው ሞት መሆኑን ባለቅኔው ይገልጣሉ ።

## 240 መወድስ

ዘተከለ ጽዮን (አለቃ)

ሞተ ዘካርያስ አብ በአፍቅሮ ወልዱ
ወሞተ የዋህ አቤል በአፍቅሮ ብእሲት ከንቱ ፤
አፍቅሮ ብእሲት ወወልድ እስመ ቀታሌ ነፍስ ውእቱ ።
በይነ ምንት ዳዕሙ ለዮሐንስ ሞቱ ?
በገዳም እንዘ አልቦቱ
ብእሲት ወወልድ እስመ ውስተ ገዳም ንብረቱ ።
ወልድሰ ወብእሲት እመ ይትረከቡ ሎቱ
እምድኅነ ከመ ሙሴ ወከመ ዳዊት በእሉንቱ፤
አፍቅሮተ ብእሲት ወወልድ ከመ ኢንእመን ባሕቱ
ሞተ ሰናክሬም በውሉዱ ወሀጕለ ሶምሶን በብእሲቱ ።

### ት ር ጉ ም

የአባት ዘካርያስ ሞት ልጅን በመውደድ ነው ፤
የየዋህ አቤል ሞትም ከንቱ ሴትን በመውደድ ነው፤
ሴትንና ልጅን መውደድ ነፍስን ገዳይ ነውና ።
የዮሀንስ ሞት ግን በምን ምክንያት ነው ?
ሴትና ልጅ
በዱር ሳይኖሩት ኑሮው በዱር ውስጥ ነውና ።
ሚስትና ልጅስ ቢገኙለት ኖሮ
እንደ ዳዊትና እንደሙሴ በነዚሁ በዳነ ነበር ፤
ሴትና ልጅን መውደድን እንዳናምን ግን
የሰናክሬም ሞት በልጆቹ ነው ፤ የሶምሶንም ጥፋት (ሞት)
በሚስቱ ነው ።



### ም ስ ጢ ር

ይህ ቅኔ ሴትና ልጅ አስገዳይም አዳኝም መሆናቸውን ከገለጠ በሁዋላ ፣ በተለይ በሴትና በልጅ አማካይነት የሚመጣውን መዘዝ አደገኛነት በምሳሌ ያስገነዝባል።

### ታ ሪ ክ

ሰናክሬም የይሁዳ ንጉስ ህዝቅያስን ለመውጋት በዘመተ ጊዜ ፣ የህዝቅያስ ረዳት መልአክ ሰራዊቱን በሰፈሩበት ቦታ ፈጅቶበት ወደ አገሩ ከተመለሰ በሁዋላ ሁለቱ ልጆቹ ሶርሶርና አድራማሌክ በጣኦት ቤት ሲሰግድ የገደሉት የአሶር ንጉስ ነው ።

ሶምሶን ከሳሙኤል በስተቀር መሳፍንት ከተባሉት የእስራኤል አዳኞችና ፈራጆች የመጨረሻው ነበረ ። አባቱ የዳን ነገድ ስሙ ማኑሄ ነበረ፤ እናቱ መካን ነበረች ። ልጃቸው ሶምሶን ከልደቱ ጀምሮ ከሚያሰክር መጠጥ ፡ ጠጉሩን ከመቆረጥና ሬሳም ከመንካት የተከለከለ ናዝራዊ ነበረ ።

በዘመኑ ፍልስጥኤማውያን አንዳንዶቹን የእስራኤል ከተሞች ወስደው ይመኩባቸው ጀመር። እስራኤላውያን ግን ሊዋጓቸው አልደፈሩም ። ከዚህም የተነሳ ሶምሶን በተሰጠው ልዩ ብርታትና ሃይል ይቃወማቸው ነበር እንጂ እንደ ሌሎቹ የእስራኤል መሪዎች ሰራዊት ሰብስቦ አልተዋጋም ። አስቀድሞ በፍልስጥኤማውያን ላይ የጠብ መነሻ ምክንያትን በመፈለግ አንዲት ፍልስጥኤማዊት ሴት አገባ ። በእርሷም ምክንያት በተጣሉ ጊዜ አዝመራቸውን አቃጠለ ብዙ ፍልስጥኤማውያንንም ገደለ ። ወገኖቹ የይሁዳ ሰዎች ፍልስጥኤማውያንን ፈርተው አሳልፈው ሊሰጡት ተስማሙ ። ሶምሶን ግን በአህያ መንጋጋ ከጠላቶቹ አንድ ሽህ ሰው ገደለ። ለ20 አመት ያህል የእስራኤልን ህዝብ አስተዳደረ ።

አንድ ጊዜ ጠላቶቹ በጋዛ ከተማ ሊይዙት ሲጠባበቁት የከተማይቱን በር መዝጊያ ነቅሎ አመለጠ ። ነገር ግን በመጨረሻው ራሱን ካለመግዛቱ የተነሳ ደሊላ የተባለች ሴት ናዝራዊነቱን እስኪ

www.ethiopianorthodox.org

### ም ስ ጢ ር

አይነ ስውር የነበረ ጦቢትን ሩፋኤል የተባለው መልአክ በሰው አምሳል መርዳቱን አስታውሰው ፣ እንደዚሁም በጎንደር ከተማ ሩፋኤል አፄ በካፋን የሚረዳቸው መሆኑን ባለቅኔው አመስጥረዋል ።

### ታ ሪ ክ

መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል ጦቢትን በሰው አምሳል እየረዳው ሰባት አመት ኑሯል ። ይኸው ጦቢት የሞተ ሰው ሳያስቀብር እህልና ውሃ አይቀምስም ነበር ። አንድ ቀን በግንብ ተጠግቶ ሙት ሲያስቀብር አንዲት ወፍ በአይኑ ውስጥ ኩሶችበትና በዚህ የተነሳ አይኑ ጠፋ ። መልአኩ ቅዱስ ሩፋኤል የአሳ አሞት አይኑን ቀብቶ አዳነው ይባላል ። በዚሁ መልአክ ስምም በጎንደር ከተማ የተሰራች ቤተ ክርስቲያን አለች ። «ዛቲ ቤትከ» የተባለችው በጎንደር ከተማ ያለችው ይችው የሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን ናት (ስንክ.ጳጉሜ 3 ቀን) ።

## 250 ሥላሴ

ዘሐይመት (ወይዘሮ)

ለወድሶትከ
ናሁ አብጻሕኩ ዐቅመ ውርዛዌ
እንዘ ብእሲት አነ እምኀይለ ውርዛዌ ድክምት
ዳዊት ጸዋሚ እመርገም ኀብስት ፤
ለዳዊትኒ አቡከ ነጋሢ መሠረተ ኵሉ መንግሥት
በፈለገ ዔላ ፈለገ ቅስት
አመ ተወርዘወ ቅድመ በወሬዛ ጌት
ወደሳሁ ከማየ አንስት ።



### ት ር ጉ ም

ከመርገም /እንጀራ
ፁዋሚ ዳዊት ! ከጉርምስና / ሃይል
የደከምሁ እኔ ሴት ስሆን አንተን ለማመስገን
እነሆ የጉልምስናን ልክ (አካለ መጠን) አደረስሁ ፤
የመንግስት ሁሉ መሰረት የሆነ ነጋሽ አባትህ ዳዊትንም
የክርክር ወንዝ በሆነ በኤላ ወንዝ
ቀድሞ በጌት ጎልማሳ ባየለ ጊዜ
እንደእኔ ሴቶች አመሰገኑት ።

### ም ስ ጢ ር

ትንሽቱ ስታድግ አካለ መጠን እንደምታደርስ ፣ ወይዘሮ ሀይመት የጎንደር ንጉስ ዳዊትን ለማመስገን የቅኔ ችሎታ ማግኘታቸውን ና ፁዋሚም ሰው ከመብል ተከልክሎ እንደሚውል ፤ አፄ ዳዊት ከህዝብ ርግማን የራቀ መሆኑን ዳዊት ጎልያድን ገድሎ በተመለሰ ጊዜ «ዳዊት እልፍ ገዳይ ሳኦል ሺህ ገዳይ» እያሉ የእስራኤል ንጉስ ዳዊትን በአመሰገኑት ሴቶች አንፃር ቅኔያቸውን አመስጥረዋል ።

## 251 ሥላሴ

ዘጕሹ አራት ዐይና

ኢያድኅነ ንዴተ ሥጋ
ተዋሕዶተ ቃል ምስለ ሥጋነ
አመ ሐተትነ በልብ እንበለ ማኅየዊ ቅብዐት ፤
ወኢይኩን በዐውደ ሮምያ በይነዝ ሁከት ፣
ይክልኑ በእግር ተሐውሶ ኀበ ፍኖተ ላዕል ወታሕት
ነፍስ ዘአልቦ ሥጋ ምውት ?
ወጽልመተኑ ያሴስል እምዐይን ማኅቶት
ዘላዕሌሁ ኢሀለወ ዘይት ?



www.ethiopianorthodox.org

የሚያነቃው የእግር ሸሆና /ደሮን ቢያጣ ፥
የሁሉ አስፈሪ የሰማዮች መንገድ / ሌሊትን
በስድስቱ የኪሩቤል ክንፎች/ ኮከቦች ለካ ።

## ም ስ ጢ ር

ደብተራ የብር ፀናፅልንና የቀንድ መቋሚያን ለማህሌት ስራ በገንዘቡ እንደሚገዛ ፃድቅ ተክለ ሃይማኖት የፀጋ ክንፍ አበቀሉ ፥ የቀንድ እግርን በተሰበረው እግራቸው ተኩ ይላሉ ባለቅኔው ።

ካህንም ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በእኩለ ሌሊት እንደሚነሳ ተክለ ሃይማኖት ባንድ እግር መቆማቸውን የቅኔው ምስጢር ይገልጣል ። ከዚህም ሌላ የሌሊት መንገደኛ የከዋክብትን መውጣት ተጠባብቆ በከዋክብት ብርሃን እያየ እንደሚሄድ ፥ የተክለ ሃይማኖትም አንድ እግራቸው ቢሰበር በስድስት የፀጋ ክንፎች ወደ ሰማይ አረጉ በማለት ባለቅኔው ለተክለ ሃይማኖት ተፈፅሟል የሚባለውን ተአምር በቅኔያቸው ምስጢር ያስረዳሉ ።

# 263 መወድስ

### ዘአፈ ወርቅ ዘውዴ (አለቃ)

ተበቃሊሁ ለሰብእ ንዋየ እዴሁ ፤
እስመ በዓለ ወርቅ ወርቅ ተፈትነ በእሳት ፥
ወአመ በምድርነ ከብደ ቅንየተ ሮሜ ክረምት
ለኵሉ ርኩብ ማየ መከራ
እስከ ኀርየ በዓለ ንዋይ ተጽናሰ እምሀብት
ወእስከ ኢክህለት ትትከበት
ንዋየ ቅድስት ሀገር እንተ መልዕልተ ደብር ተሐንጸት።
ወእምላዕል ዘይዘንም ወዘይነቅዕ እምታሕት
ማየ አይኅ አማዕበለነ በመዓልት ወበሌሊት ፤
ወእማየ አይኅ ንድኅን ኢትጹረነ ታቦት
ታቦትነ አራራተ ለርእሳ ኢረከበት ።



## ት ር ጉ ም

ሰውን የሚበቀለው የእጁ ገንዘብ ( የገዛ ገንዘቡ) ነው፤
ባለ ወርቅ / ወርቅ በእሳት ተፈትኗልና ፥
የሮም አገዛዝ / ክረምትም በምድራችን በከበደ ጊዜ
ፈተና / ውሃ ለሁሉ ግኝ ነውና ( ይገኛልና )
ባለገንዘብ ከሀብት ይልቅ ችግርን እስከ መረጠ ድረስ ፥
በደብር ላይ የታነፀች
የተለየች ( የከበረች ) ታቦት እቃም ልትደበቅ እስካልቻለች ድረስ ፤
ከላይም የሚዘንብና ከታች የሚፈልቅ ( የሚመነጭ ) የጥፋት ውሃ
በቀንና በሌሊት አጥለቅልቆናልና
ከጥፋት ውሃም እንድን ዘንድ ታቦት እንዳትሸከመን
ታቦታችን አራራትን ለራሷ አላገኘችምና ።

## ም ስ ጢ ር

በጠብመንጃው ቃታ ያጎረሰው ጥይት ተባርቆ ባለጠብመንጃውን እንደሚመታው ሁሉ ባለወርቅና ብር ደክሞ በላቡ ባፈራው በገዛ ገንዘቡ ተሰቃየ ። ወርቅም በእሳት እንደሚፈተን ባለብር በእሳት በጋለ ብረት ምጣድ ተጠበሰ ።

ክረምትም በምድር ላይ እንደሚከብድ የሮም ፋሽስት አገዛዝ በኢትዮጵያ ላይ አለወጉ ሆነ ። ክረምትም በከበደ ጊዜ ውሃ በየደጁ ለሁሉ እንደሚገኝ በሮም አገዛዝ ጥናትም መከራ ለሁሉም ደረሰው ። ክረምት ሲከብድ ፀሀይ እንደሚፈለግ ፥ በኢጣልያ አገዛዝ ሽፍታውም ባንዳውም ባለገንዘቡን ሲያሰቃዩት ባለፀጋው « ምነው ድሃ በሆንሁ » እስከማለት ደረሰ ።

በተራራ ላይ የተሰራች መንደር ከአይን እንደማትሰወር በየደብሩ በቤተ ክርስቲያን የተኖረው የታቦት እቃ ሁሉ ተበረበረ (ተዘረፈ)።



www.ethiopianorthodox.org

በኖህ ዘመን ከላይ የዘነበውና ከምድር የመነጨው የጥፋት ውሃ የቀድሞ ሰዎችን በቀንና በሌሊት እንዳሰጠማቸው በኢጣልያ ወረራ ጊዜ በቀን ባንዳዎች ፥ ሽፍቶችም በሌሊት ህዝቡን ደበደቡት ። የጥፋት ውሃ ከላይ ወደ ምድር እንደዘነበና ከምድርም ወደላይ እንደፈላ ከአውሮፕላን ላይ ቦምብ ወደህዝቡ ተጣለና ምድሩን አደባለቀው ፥ የላዩን በታች የታቹን በላይ አደረገው ፤ ስለዚህም ሌትም ቀንም መባነን ሆነ ።

ኖህ ከእነቤተሰቦቹ በታቦት ( በመርከብ) ወስጥ ገብቶ ከጥፋት ውሃ እንደዳነ ፥ የኢትዮጵያ ህዝብ በቤተ ክርስቲያን ታቦት ከኢጣልያ አደጋ እንዳያመልጥ የቤተ መቅደስ ታቦት ለራሷ መጠጊያ ደብርን አላገኘችም ። ምክንያቱም ደብሩ (ቤተ ክርስቲያኑ) ከአውሮፕላን ላይ በሚወረወር ቦምብ ከመደብደብ አላመለጠምና ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

## ታሪክ

ይህ ቅኔ የተደረሰው ከጎጃም አድባራት መካከል አንዱ በሆነው በደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ነው ። ዘመኑ 1931 አ.ም. ሲሆን ፥ ምክንያቱ ጠላት ከ1928 አ.ም. ጀምሮ በኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ስለፈፀመው ግፍ ነው ። በዚያ ዘመን ስለሀብት መኖር ጭምጭምታ የተሰማበት ሰው ሁሉ ቀን ቀን በኢጣልያ ፋሽስት ባንዳ ሲደበደብና ሲሰቃይ ይውላል ። ሌሊት ሌሊት ደግሞ በሽፍቶች የቀበርኸውን ብር አምጣ እየተባለ የፊጥኝ ከወጋግራ ጋር ታስሮ ይገረፋል ፤ በእሳት በጋለ ብረት ምጣድ ላይ ተቀምጦ ይጠበሳል ። ያን ጊዜ ያልተሰቃየ ከስንት አንድ ነው ፤ በቤቱ የሚውል አልነበረም።መላው ቤተሰብ በጫካና በዋሻ ውሎ ማታ ጨለማ ለብሶ እቤቱ ገብቶ ቤቶቹ እሳት ሲያጢያጢሱና ገና እህል ሳይቀምሱ ሽፍታ በየቤቱ ከች ይልባቸዋል ። በአርበኞች ሰፈር አካባቢ የነበሩት ቤተ መቅደሶች ከአውሮፕላን ላይ ቦምብ ተጣለባቸው ። የታቦት እቃ ቤቶችና መቅደሶችም ተበረበሩ ። የየደብሩ ህዝብ በሙሉ በባለሳንጃ ፈረሰኞች ፋሽስቶችና ባንዳዎች እየተከበበ መሳሪያው ቀርቶ ቀለህ የተገኘበት ይረሸን ነበር ።



## 264 መወድስ

ዘውብሽት (መምህር)

ለዐዕመ ልዳዊ ሰማዕት እግዚእ ተገፍዖ
ይስቅልዎ መጽኡ አይሁድ ነፋሳት ፥
ወዝርዋነ ምድር ኮኑ ሕዋሳቲሁ አርድእት ፤
ለሞት አምጣነ አብጽሖ ይሁዳ መጥባሕት ።
ወአመ ተምዑ አጋዕዝት
ሕንጸ ሥጋሁ ሰናዖር በነፋሰ ዐውሎ ተመዝበረት ።
ፈረየትሂ ለሰዕለቱ አስካለ ምትረት
ከሣደ ጊዮርጊስ ዕፀ ከርካዕ ኀበ ሙሐዘ ማይ ዘበቈለት፤
አመኒ ደወየ በዂረ ተጋድሎ ሰማዕት
መጽኡ ለጠይቆ አዝማደ ጳውሎስ አክሊላት ።

## ትርጉም

የመገፋት ጌታ / የልዳ ሰማእት አጥንትን
ይሰቅሉት ዘንድ ነፋሶች / አይሁድ መጡ ፤
ተማሮች/ ሰውነቶቹም የምድር ብትኖች ሆኑ ( ተበተኑ ) ፤
ይሁዳ / ሰይፍ ለሞት አድርሶታልና ።
ጌቶችም (ስላሴ) በተቆጡ ጊዜ
የስጋው / ሰናኦር ህንፃ በአውሎ ነፋስ ፈረሰች ።
በውሃ መውረጃ የበቀለች የጊዮርጊስ
አንገት / የሎሚ እንጨትም ፍሬ/ መቆረጥን በየቀኑ አፈ
ራች ፤
የመጋደል አለቃ / ሰማእትም በታመመ ጊዜ
የጳውሎስ ዘመዶች / አክሊሎች ለመጠየቅ መጡ ።



www.ethiopianorthodox.org

## 266 ሚበዝኊ

ዘተክለ ጽዮን (አለቃ)

ሐሜተ ክልኤቱ አኀው
ዘኢፈርሀ ወልድ በልዐ በተከብቶ
ሥጋ ጥዑመ እንዘ የዐጹ ኆኅቶ ፤
ወፍሉጠ ሞት ኮነ ባሕቲቶ ዘበልዐ እስመ ይመውት
ባሕቲቶ ።

ት ር ጉ ም

የሁለቱ ወንድሞቹን አሜት
ያልፈራ ወልድ በሩን ዘግቶ
በመደበቅ ጣፋጭ ስጋን በላ ፤
በሞትም ልዩን ሆነ «ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታልና።»

ም ስ ጢ ር

የባልጀሮችን አሜት ያልፈራ ሰው ደጃፉን ዘግቶ ስጋን እንደ ሚበላ ከሶስቱ አካላት አንዱ አካል ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ በቦታ ሳይለይ በተለየ አካሉ የማርያምን ስጋ ለበሰ ፤ በድን ግልናም ተወለደ ። « ብቻውን የበላ ብቻውን ይሞታል » እንዲ ሉም ወልድ በለበሰው ስጋ ሲሞት ፣ አብና መንፈስ ቅዱስ ስጋን ባለመልበሳቸው በሞት አልተሳተፉትም ( እንደ ወልድ አልሞቱም) በማለት ባለቅኔው የወልድን ሰው መሆንና መሞት ያስገነዝባሉ ።

## 267 ግእዝ ጉባኤ ቃና

በካፋ ኢትርሳዕ ዘተዋነይነ ክልኤነ ፤
እንዘ አበ አብርሃም አንተ ወብእሲተ አብርሃም አነ ።



ት ር ጉ ም

በካፋ ! ሁለታችን የተጫወትነውን አትርሳ ፤
አንተ የአብርሃም አባት (ታራ) ስትሆን እኔም የአብርሃም
ሚስት (ሳራ) ስሆን ።

ም ስ ጢ ር

ሁለት ጓዶች ሲጨዋወቱ ቆይተው ሲሰነባበቱ አንዱ ለሁለ ተኛው «ያን የተባባልነውን እንዳትረሳ» ይለዋል ። በዚህም አንፃር አፄ በካፋ በልጅነታቸው ከአንድ ጓደኛቸው ጋር በትምህርት ቤት ሲማሩና አፍአ ወጥተው (ተቀምጠው) ሳሉ «እኔ ብነግስ አንተንም ሾሜና ሸልሜ አልቅሃለሁ» የሚል የልጅነት ተምኔታዊ ተስፋ ለዚሁ ጓደኛቸው ሰጥተው ነበር ። አፄ በካፋ በምኞታቸው መሰረት ለመን ግስት በቁ ። ያም ተማሪ ምሁር ሆኖ ወደ ንጉሱ (አፄ በካፋ) ቀርቦ ያን በአፍአ የተጨዋወቱትን የልጅነታቸውን ነገር በዚህ ቅኔ አማ ካይነት አስታወሳቸው እና ያሉትን ፈፀሙለት ይባላል ።

## 268 ዋዜማ

ዘኀይሉ ( ዘመቀሉ )

ጽዮን ኢየአምሮ
መሰግላዊ አጽሎን እንተ ያሰግድ አእባነ ፣
ሶበ ሰትየ በቀርነ ኢሎፍሊ መጓተኪ ወይነ
ልብሰ ከዊኖቱ አምላከ እስመ ኀደገ ፍጡነ ፣
ወእንዘ ለሕዝቡ ይብሎሙ መድኀኒት አነ
መድኀኒተ ለርእሱ ኢኮነ ።

ት ር ጉ ም

ፅዮን ድንጋዮችን
የሚያሰግድ የጠንቋይ ወገን/አጽሎን አያውቅም ፣
መአትሽ/ወይንን በኢሎፍሊ/ዋንጫ በጠጣ ጊዜ



www.ethiopianorthodox.org

ት ር ጉ ም

የመዳኛ መስዋእት/ ሰይፍ ቢሰዋ
ህያዋንንና ሙታንን በደሙ አዳነ ፤
ስጋ ከለበሰና እንደኛ ከሆነ በሁዋላ
የይስሀቅ ሞት/ ስልጣንን በደሙ አጥፍቷልና ፣
የሌለን እኛም
በግብፅ የሶስትነቱ ምስጢር አንድነትን አላየንም ።
በስጋ ርስት ግን ያላየነውን የሰይፍ ሞት አየን ፤
ለቃል የሆነው ለስጋ ሆኗልና ።
የሰይፍም ውበቱ የሰማዮች ጨረቃን ከደነ (አለበሰ) ፤
ጨለማንና ብርሃንን በሰማይ ፈጥሯልና ።

ም ስ ጢ ር

አብርሃም ልጁን ይስሀቅን ለእግዚአብሄር ሊሰዋበት የቃጣው ሰይፍ ደም ተቀብቶ በመገኘቱ ይስሀቅ ከመሰዋት ዳነ ። ክርስቶስ ስጋን ለብሶ እንደእኛ ሰው እንደሆነ የአብርሃም ሰይፍ የሰማያዊ በግ አንገትን በይስሀቅ ፈንታ ቆረጠ ። የእግዚአብሄር ቃል ርስት (አምላክነት) የስጋ ገንዘብ እንደሆነ ይስሀቅ እንዳይሰዋ ከሰማይ ቃል ተሰማ። ብርሃንም ሰማይን እንደሚያደምቀው በአብርሃም ሰይፍ የታየ ደም በሰማይ ጨረቃ ታየ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

# 272 ሕንጼሃ

ኦንከ ቀራንዮ ኢይበጽሕ እግዚእነ ፤
እስመ ቀራንዮ ምድረ ደም ኮነ ።

ት ር ጉ ም

እንግዲህ ጌታችን ቀራንዮ አይደርስም ፤
ቀራንዮ የደም ምድር ሆኗልና ።



www.ethiopianorthodox.org



ደመኛ ያለው ሰው ደም ወደፈሰሰበት ቦታ መሄድ ያስፈራዋል ፤ እንዲሁም ደሙ በቀራንዮ የፈሰሰ ክርስቶስ በዚያ እንደሞተ አለመቅረቱና ከመቃብር መነሳቱ በቅኔው ተመስጥሯል ።

# 327 መወድስ

ዘጉባይ ( አለቃ )

ሞተ ፍጡራን ተምህረ ገቢረ ትሕትና
አንቃዕዲዎ ኢይርአይ ገጸ አረጋዊ በዐይኑ ፤
ባሕቱ ይብለነ ውስተ ደብረ ዳሞ መካኑ ።
እንበለ ውእቱ አረጋዊ
ሥጋ ሰብእ ለቢሶ ዘሞአኒ መኑ
ንንግር ወንዜኑ ፤
ከመ ከመ ሊቁ ኤልያስ ለአረጋዊ መጠኑ ።
ለሕያውኒ ገብረ ክርስቶስ ላእካነ ምስጢር ኮኑ
ካህናተ ሰማይ ሕማማት መንበረ ሥጋሁ ዘየዐጥኑ ፤
ወእምሐዋርያት ገድላት እለ ተአመኑ
ዮሐንስ ዕፄ ሥጋ ዘረፈቀ ውስተ ሕፅኑ ።

ት ር ጉ ም

ቀና ብሎ የሽማግሌ ፊትን በአይኑ
እንዳያይ የፍጡራን ሞት የትህትና ስራን ተማረ ፤
ነገር ግን በደብረ ዳሞ ቦታው ውስጥ
ያለዚያ አረጋዊ
«የሰው ስጋ ለብሶ ያሸነፈኝ ማን ነው ?» ይለናል ፤
የአረጋዊ መጠኑ
እንደ ሊቁ / ኤልያስ እንደሆነ እንናገርና እናወራ ዘንድ።
ስጋ / መንበሩን (ዙፋኑን) የሚያጥኑ ህማሞች / የሰማይ ካህናትም ።

ሶበ ዘበጠ ዝናመ ዜና
መሬት ጸገየ እምላክና
ወእምላክ ፈረየ ሰብእና

ትርጉም

በቀድሞ ዘመን
በሙሴና በሚካኤል ሹመት ጊዜ
የእረታቸው ተረከዝ የመጀመሪያ ዱካን (ፍለጋን) አል
ቀረፀም ፤
በሌላ መንገድም አልለያቸውም ፤
በገብርኤል ሹመት / የቃሉ ደመና ክረምት ግን
ዝናብ / ወሬ በመታ (በጣለ) ጊዜ
መሬት እምላክነትን አበበ ፤
እምላክም ሰው መሆንን አፈራ ።

ምስጢር

ሙሴና ሚካኤል እስራኤልን እየመሩ በመገቡበት (በአስተዳደሩበት) ዘመን አንበሳ የእግሩ ርግጫ ዱካን (ፍለጋን) እንደሚያጠፋ የሙሴ ሁኔታ በሚካኤል ፤ የሚካኤልም ሁኔታ በሙሴ አልተመለከተም ነበር ። በገብርኤል ቃል ምግብና (ማገልገል) ጊዜ ግን በክረምት ደመና ጠል የረካ የመሬት ተክል አበባን እንደሚያብብና ዝሪቱም (ሰብሉ) እንደሚያፈራ ከመሬት የተፈጠረው ሰው እምላክነትን ፤ እምላክም ሰው መሆንን ተገናዘቡ (ገንዘብ አደረጉ) ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

## 277 ሥላሴ

ዘእንግዳ ወርቅ ኀይሉ ( አለቃ )

በቀለ ቀዳማዊ
በአፍአ እጥፍኡ እማእከሎሙ
አርዌ ምድር ወቶማስ ክልኤቱ ዘተባእሱ በዜና ፤



ወሞእዎ ዓዲ ለእኩይ ሕሊና ፤
ላዕለ አርዌ ምድር ቶማስ እዴሁ ከመ ኢያንሥእ በፍና
እእዳው ለቶማስ እስመ ኢኮና ፤
ወኢይዕቀብ አርዌ እእጋረ ጊዜ ጽሙና
ኢሀለዎ ለቶማስ ሰኰና ።

ትርጉም

በወሬ የተጣሉ
ሁለቱ ቶማስና የምድር እባብ
የቀድሞ በቀልን (ቂምን) በመካከላቸው አጠፉ ፣
ዳግመኛም «ክፉ አሳብን አሸነፉ» ፤
በምድር እባብ ላይ ቶማስ እጁን በመንገድ እንዳያነሳ
እጆቹ ለቶማስ አልሆኑምና ፤
እባብም እግሮችን በድካም ጊዜ እንዳይጠብቅ ( እንዳይ
ነድፍ )
ለቶማስ ተረከዝ የለውምና ።

ምስጢር

በመሬት ተጣልተው የኖሩ ሁለት ሰዎች ሲታረቁ «አንተም በእገሌ ይዞታ የሚያገባህ የለም ፤ አንተም ደግሞ ከእገሌ ይዞታ ምንም የለህ ፤ ስለዚህ ቂም በቀላችሁን ተዉ» ይባላሉ ። እንዲሁም አዳም የእባብን ራስ በበትር እንዲቀጠቅጥና እባብም ተረከዙን እንዲነድፈው በተደረገው መሰረት በሰውና በእባብ መካከል ያለው ቅራኔ በቶማስ ሁኔታ ለእባብ ጠፋለት ። ቶማስ እባቡን በእጁ በትር እንዳይቀጠቅጠው እጆች የሉትም ፤ እባብ ደግሞ እግሩን እንዳይነድፈው የቶማስ እግሮቹ ተቆርጠዋል ። ስለዚህ «ሲስኑ ይሰለቡ» እንዲሉ ባለመቻላቸው ብቻ ከአንገት በላይ ቶማስና እባብ ተስማሙ ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።



www.ethiopianorthodox.org

ነው ። ቅዱስ ገብርኤልም ኤልሳቤጥ በፀነሰች በስድስተኛው ወር ወደገሊላ ሄዶ ማርያምን «በድንግልና ትወልጃለሽ» ብሎ እንዳበሰራት ለንጊኖስ የተባለ አንድ አይና ወታደር የክርስቶስን ጎን በጦር ቢወጋው የደሙ ፍንጣቂ የነካው እውሩ አይኑ በራለት ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## 280 ሥላሴ

ዘኮብቱ (ዐቃቤ ሰዓት)

መንግሥተ ሰማይ
ኀቤሁ ለጴጥሮስ እንዘ ቅርብት
ኢነጽረ ጴጥሮስ ኪያሃ ተሥዕሎተ መልክአ ብርሃን
እስከ ተፈጸመ በታቦር ማሕፀን ፤
ከመሰ ኢንበል እመ ይቀርብ መካን
ነጽሮ ቅሩበ ኢይሰእን ፥
ቀራንብት ለዐይን እንዘ ቅሩባን
ቀራንብተ ኢይኔጽር ዐይን ።

ት ር ጉ ም

መንግስተ ሰማይ
ወደጴጥሮስ የቀረበች ስትሆን
የመልክ ብርሃን መሳል በታቦር ማህፀን
እስከ ተፈፀመ ድረስ ጴጥሮስ እሷን አላየም ፤
ቦታ ቢቀርብ ቅርብ ማየት
አይሳንም እንዳንል ግን ፥
ቅንድቦች ለአይን ቅርቦች ሲሆኑ
ቅንድቦችን አይን አያይም ።





ሰዎች በፍቅር ቅርበት እንጂ በቦታ ቅርበት ሊጠያየቁና ሊተያዩ አይችሉም ። እንዲሁም ቅዱስ ጴጥሮስ የመንግስተ ሰማይ መክፈቻ የተሰጠው ሲሆን ዝንን ከፍቶ ሊገባባት አልቻለም ። የአካል ቅርፅ በማህፀን እንደሚፈፀም ጴጥሮስም የመንግስተ ሰማይ በር አርአያን በደብረ ታቦር አየ እንጂ ፥ በቦታ መቅረብማ ማየት ከተቻለ አይኖች ቅንድቦችን ያዩ ነበር በማለት ቅኔው ተመስጥሯል።

## 281 ሥላሴ

ዘገብረ ሥላሴ (መምህር)

አእላፍ የሐምይዎ
ለኪሩብ ካህን እንዘ ንጹሕ
ከመ እምኔሁ ተወልደ በሥጋ ተክለ ሃይማኖት መድኅን
ለውእቱ እስመ ይመስሎ በመልክአ ወሥን ።
ወትእምርተ ዝንቱ ተረክበ በኀበ ተክለ አብ ሕፃን
እመንገለ ፀጋም ወየማን ፥
ወከመ ኪሩብ ቀሲስ በሊሐ ልሳን ፤
ወመጠኑ ዘኪሩብ መጠን ።

ት ር ጉ ም

አዳኝ ተክለ ሃይማኖት
በስጋ ከርሱ እንደተወለደ
ንፁህ ሲሆን ኪሩብ ካህንን ወገኖች ያሙታል ፤
በመልክና በደም ግባት እርሱን ይመስለዋልና ።
የዚህ ምልክትም በስተግራና በስተቀኝ በኩል
በተክለ ሃይማኖት ህፃን ዘንድ ተገኝቷልና ፥
እንደ ኪሩብ ቄስም አንደበተ ርቱእ ነውና ፤
ልኩም የኪሩብ ልክ ነውና ።



www.ethiopianorthodox.org

የሆነበት ምክንያት ከእለታቱ በአንዱ ቀን ሰሎሞን አንድ የራበው ድሃ ሲለምን አይቶ «ምንድን ነው?» ብሎ ጠየቀ ። ቤተሰቦቹም የተራበ ለማኝ ነው አሉት ። እርሱም « ራብ ምንድነው?» ብሎ ጠይቆ ነበርና እንዲቀምሰው እግዚአብሄር ይህን ችግር እንዲደርስበት አደረገ ተብሎ ይተረካል ።

## 288 መወድስ

በይነ ምንት ኀፍሩ ነቢያተ ሕግ ?
እምጣነ እምዓለም ተኀጥኡ ድኅረ ጸውዑ እግዚአ
እንዘ ይረድኦሙ ኤልሳዕ በነሢአ ልሕኵት ዘመጽአ ።
ወይኤዝዝ ዮሴፍ መገብተ ቤቱ
ለአስተዳልዎ ሠናየ ጽዋዐ ፤
ወከመ ያሠኒ ቤተ መርዓ
ምስለ መሰንቆሁ ዳዊት እማእከሎሙ ተንሥአ ።
በዓሎሙሂ ትንቢተ ሕግ ለእመ ኮነ ርቱዐ
ኢኀጥኡ ለተጠብሖ ላሕመ ወበግዐ ፤
ለተሣይጦ ላሕም ሄኖክ እምጣነ እምገዳም ወፅአ
ወበይነ በግዑ ኢሳይያስ ቃለ ኢያውሥአ ።

### ት ር ጉ ም

የህግ ነቢያት ስለምን አፈሩ ?
ገንቦን በመያዝ የመጣ ኤልሳእ እየረዳቸው
ጌታን ከጠሩ በሁዋላ ከአለም ታጥተዋልና ።
ዮሴፍም የቤቱን መጋቢዎች መልካም
መጠጫን ለማዘጋጀት ያዝዛል ፤
የሙሽራ ቤትንም ያሳምር ዘንድ
ዳዊት ከመሰንቆው ጋር ከመሃላቸው ተነሳ ።
በአላቸው/ የህግ ትንቢትም የተቃና ቢሆን
ለመታረድ በግና ላምን አላጡም ፤
ሄኖክ ላምን ለመግዛት ከገዳም (ከጫካ) መጥቷልና
ስለበጉም ኢሳይያስ ቃልን አልመለሰምና ።



### ም ስ ጢ ር

ያላቅማቸው ጌታ ሰውን ለግብዣ የጠሩ ጋባዦች በተጠሪው ፊት ቀርበው ለመጋበዝ ያፍሩና ውጭ ለውጭ ይላሉ ። ስለወልድ ወደዚህ አለም መምጣት ሲግልጹና ሲተነቡ የኖሩ ነቢያትም ወልድ ስጋን በለበሰበት ዘመን አልተገኙም በሞት ተለዩ ። ደግሞ በድግስ ቀን የደጋሹ ረዳት መጠጡን በገንቦ እንደሚያቀርብ ነቢዩ ኤልሳእ ቅድስት ማርያምን በገንቦ መስሎ ተናገረ ። ሌላውም የጠላ መጠጫ እቃ ለማዘጋጀት ቤተሰቦቹን እንደሚያዝ እርሱዋ (ማርያም) በዮሴፍ ፅዋ ተመሰለች ። የሰርግ ቤትንም ለማድመቅ ከተጋባዦች መካከል አንዱ እንደሚነሳና በመሰንቆ እንደሚዘፍን በዳዊት መሰንቆም ድንግሊቱ ተመሰለች ። ደጋሾች ሀብት ያላቸው ከሆኑ ለድግሱ የሚታረድ በሬና በግ እንደሚገዙ ትንቢታዊ ምሳሌም ልዩ ልዩ በመሆኑ ፣ ክርስቶስ በኢሳይያስ ትንቢት በሚታረዱ በሬና በግ ተመሰለ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## 289 ዕዝል ክብር ይእቲ

ሚካኤል ኀዘንከ ለርኁባን መጠነ ዓመታት አርብዓ ፤
ወበተአዝዞ ከረይከ መቃብረ ሙሴ ኀቡአ ።
ባዕልሰ ይትፌሣሕ ሶበ ዜና ረኃብ ሰምዐ ፤
ወመቃብረ ይከሪ ለወርቁ እንዘ በድነ ቢጹ በአፍአ ።

### ት ር ጉ ም

ሚካኤል ! ለተራቡ አርባ አመታት ያህል አዘንህ ፤
በመታዘዝም ድብቅ የሙሴ መቃብርን ቆፈርህ ።
ባለፀጋ ግን የራብን ወሬ በሰማ ጊዜ ይደሰታል ፤
የጓደኛው በድንም በውጭ ሳለ ለወርቁ መቃብርን ይቆፍራል።



www.ethiopianorthodox.org

### ም ስ ጢ ር

ቅዱስ ሚካኤል እስራኤልን በሙሴ አማካይነት ከግብፅ አውጥቶ እየመራቸውና መናን እየመገባቸው አርባ ዘመን ሙሉ አብሯቸው እንደተጓዘ ፣ አንዳንድ ርህሩህ ሰው ብዙ ጊዜ ራብተኞችን ሲያበላና ሲያጠጣ የሞተውንም ወሰንተኛ (የሌላ አገር ሰው) ሲቀ ብር ይኖራል ። ሌላው ጨካኝ ግን ዘመኑ የራብ ዘመን ሲሆንለት ብርን ለማፈስ ይደሰታል ፤ ድሃውም በራብ ሞቶ በድኑ በውጭ ወድቆ እያየ ፣ የሞተውን ድሃ በመቅበር ፈንታ ወርቁን በመሬት ውስጥ ይቀብራል በማለት ባለቅኔው የባለፀጎችን ጭካኔ በቅኔያቸው ምስጢር አመልክተዋል ።

## 290 መወድስ

ገሠጽኮ ለዮናስ በቀስታመ ባሕር
ኅበ ኢዘርዐ ሰብከተ ኀጠተ ቃሉ ዘራዒ
በምድረ ነነዌ ፀርከ በገራህተ እዝና ሰማዒ ፣
ወበቃለ ረኃብ ተዛለፍኮ
ለዘኢኀዘነ ኤልያስ ቀናኢ
በእሳተ ረኃብ እንዘ ያውዒ
ዙሎ ገዳመ ቤተ አክዓብ ገፋዒ !
አኮኑ አምላኩ ፍቅር ! እንዘ ነደ እሳት በላዒ
ትቄርር ከመ ማይ ድንጋጼ ኀጥአን ሶበ ትሬኢ ፣
ለገብርከኒ ዓለም በበትረ መከራ በቃዒ
ተግሣጸ ውሉድ ትጌሥጽ ወኢትሬእዮ ከመ ጸላኢ ።

### ት ር ጉ ም

በጠላትህ /ነነዌ ምድር ሰሚ
ጆሮዋ/ እርሻ የዘሪ ቃሉ ቅንጣት/ ስብከትን
ካልዘራ ዘንድ ዮናስን በዱላ /ባህር ቀጣኸው ፣
ገፊ የሆነ የአክአብ



www.ethiopianorthodox.org

ወገን /ጫካውን ሁሉ
በእሳት /ራብ ሲያቃጥል
ያላዘነ ቀናተኛ ኤልያስንም በቃል/ ራብ ዘለፍኸው ፤
የፍቅር አምላክ ! አቃጣይ የእሳት ነዲድ ስትሆን
የሀጢአተኞችን ድንጋጤ ስታይ እንደውሃ ትቀዘቅዛለህና፣
አገልጋይህ/ አለምንም በጠቃሚ መከራ /በትር
የልጆችን ቅጣት ትቀጣዋለህና እንደጠላትም አታየውምና።

### ም ስ ጢ ር

እርሻ አርሶ ዘር እንዲዘራ ያዘዘው አንደኛው ልጁ ትእዛዙን ሳይፈፅም ሲቀር አባቱ ተቆጥቶ በሸመል ይመታዋል ፤ ደግሞ በሬዎቹን ውሃ እንዲያጠጣቸው ያዘዘው ሌላው ልጁ የታዘዘውን ሳይፈፅም ሲቀርና እንኩቶም ሲያነኩት የጫካውን ሳር ሲያቃጥለው በቁጣ ቃል ይዘልፈዋል ።

እንዲሁም በአንፃሩ ዘር ያልዘራው ልጅ ምሳሌ የሆነው ነቢይ ዮናስ ነነዌን አልሰብክም በማለቱ በባህር ውስጥ እንዲሰጥምና በአሳ አንበሪ ሆድ እንዲዋጥ አደረግኸው ። በሬዎችን ያላጠጣው ልጅ ምሳሌ የሆነውን ነቢይ ኤልያስንም እስራኤልን በራብ ስላ ንገበገባቸውና ስላላዘነላቸው እንደህዝቡ እንዲራብና እንዲጠማ ምግቡን አስቀረህበት የሚጠጣበትንም ምንጭ አደረቅህበት ። በቁጣ የተናደደውን ያህል ልጆቹ ይቅርታ እየጠየቁ ሲቅለበለቡ በት አባት ከቁጣው እንደሚበርድ ፣ በሀጢአተኞች ድንጋጤ ጊዜ መአትህን በምህረት ቁጣህን በትእግስት ትመልሳለህ ማለት በቅ ኔው ተመስጥሮበታል ።

## 291 ሥላሴ

ፍናዊነ ብዙኃት
በከመ ብዙኃት አህጉሪነ ፤
ባሕቱ በጽዮን እመ ይከውን ጉባኤ

አህጉር ክልኤቱ ወፍናው ክልኤ ።
ወጊዜ ምሳሐ ለጽዮን ከመ ኢንሕሚ ጸዋዔ
ዙሉ ይጼዋዕ ጊዜ ትንሣኤ ፤
ባሕቱ ይከውን በዝንጋዔ
ኢበላዒ ዘትካት በላዔ ።

## ት ር ጉ ም

አገሮቻችን ብዙ እንደሆኑ
መንገዶቻችን ብዙዎች ናቸው ፤
ነገር ግን በፅዮን ስብሰባ ቢሆን
አገሮች ሁለት ናቸው ፤ መንገዶችም ሁለት ናቸው ።
በፅዮን ምሳም ጊዜ ጠሪን እንዳናማ
ለትንሳኤ ጊዜ ሁሉ ይጠራል ፤
ነገር ግን በመርሳት የቀድሞ
ተራቢ በላተኛ ይሆናል ።

## ም ስ ጢ ር

በዚህ አለም አገሮችና መንገዶቻቸው ብዙዎች ናቸው ። ለወዲያኛው አለም (ለእለተ ምፅአት) ጉባኤ ግን ሰፊ ቦታና መንገድ የሉትም ቦታዎቹም መንግስተ ሰማይና ገሃነም ብቻ ናቸው ፡ መንገዶችም ህይወትና ሞት ብቻ ይሆናሉ ። የሞተው ሰው ሁሉ መንገድ መንገዱን ለመሄድ ቢነሳ የበላው እንዳልበላ ፤ ያልበላውም እንደበላ ይሆናል በማለት ፤ ቀድሞ በድሃና በሃብታም መካከል ይታይ የነበረው ልዩነት ከሞት በሁዋላ የሚስተካከል መሆኑን ባለቅኔው በቅኔያቸው ምስጢር ገልጠዋል ።

## 292 ሥላሴ

ሰሚዕየ ኢይሰምዓ
ለመንግሥተ ሰማይ መዝሙረ ዕንቍ
ዘአውታሪሃ ሕማም ወድኅንፃሃ ተገፍዖ ፤



www.ethiopianorthodox.org

እስመ ተድላ ሥጋ ለሥጋየ ሞአ ፡
ባሕቱ ጴጥሮስ ብእሴ ብዙኅ ተበፅዖ
አፍቀረ ሞተ ዘይጸልእ ፡
ወእንዘ ለድምፃ ጳውሎስ ያጸምዖ
ኢያእመረ ከመ ሰይፍ በልዖ ።

## ት ር ጉ ም

አውታሯ መከራ
መቃኛዋም መገፋት የሆነ
መንግስተ ሰማይ/ የእንቁ መዝሙርን ሰምቼ አልሰማትም፡
የስጋ ምቾት ስጋየን አሸንፎታልና ፡
ነገር ግን ጴጥሮስ/ የብዙ ምስጋና ሰው
የሚጠላው ሞትን ወደደ ፡
ጳውሎስም ድምፁዋን ሲሰማ
ሰይፍ እንደበላው አላወቀም ።

## ም ስ ጢ ር

አሳቡ ወደሌላ የተሰማራበት ሰው እያለ እንደሌለ ስለሚሆን ሌላው የሚጫወተውን ነገር ልብ አይለውም ። እንዲሁም የዚህ አለም ተድላና ደስታ ያሸነፈው አለማዊ መንግስተ ሰማይን ለመውረስ የሚያስችለውን ስራ ከመስራት ወደሁዋላ ይላል ። አሳቡ የተሰበሰበለት ሰው ግን ጓደኛው የሚነግረውን ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ልብ እንደሚል ፡ በመንግስተ ሰማይ ፍቅር የተነደፈ ጴጥሮስ በህይወት ኖሮ ከመንግስተ ሰማይ ውጪ ከመሆን ስለርሷ መሞትን መረጠ ። እንዲሁም ጳውሎስ ስለርሷ (መንግስተ ሰማይ) በሰይፍ መቆረጡን ከመቆረጥ አልቆጠረውም ይላሉ ባለቅኔው ።

ሳለ የጥፋቱ ውሃ መቶው ዘመን ሲሞላ ዘነበ ። ለህዝቡ የተናገረው መቶ ሃያ ዘመን አልሆነም ። ስለዚህ ኖህ ሃያ ዘመንን አበለ ተብሏል ።

እንዲሁም ነቢይ ዮናስ «ታላቅ አገር ነነዌ እስከ ሶስት ቀን ድረስ በሰማይ እሳት ትገለባበጣለች » ብሎ ለከተማይቱ ህዝብ ሰብኮ ነበር ። ግን ህዝቡ ከእነንጉሱ ንስሃ ገብተው ስለፆሙና ስለፀለዩ የሰማይ እሳት በአየር ታይቶ ተመልሶላቸዋል ፤ ስለዚህም ዮናስ አባይ መስሎ ተገኝቷል ። እባብ አልዋሸም ማለት ግን «እፀ በለስን ብትበሉ አምላክ ትሆናላችሁ» በማለት የተናገረው ከአዳምና ከሄዋን ዘር ከቅድስት ማርያም የተገኘ ስጋ በመለኮት ተዋህዶ አምላክ ሆነ መባሉ እንደሆነ ባለቅኔው ያስገነዝባሉ ።

## 298 መወድስ

በመስፈርተ ሰሎሞን ነሥአ ሥንቀ ኢተዐውቆ
ገብረ መርዓዊ ዘሠምረ ሐዊረ ሥቃያት ፍናው ፤
እስመ በደዌ ተሰብረ ሥነ መልክኡ ማኅው ፤
ዳንኤል ልቡናሁ
እንዘ ለተሀውኮ አንበሳ ምጥው ።
ወለሥጋሁ ፈትለ ሜላት
ተካፈልዋ ሰረቅት ዕፄያት በመዳልው ።
ኀበሂ ተረክበ ትዕግሥተ ዕፄ ልብው
የዋሃን አጸብዒሁ አምለኩ በዕፀው ፤
ወእኮ ምኑን በኀቤሆሙ ለአዕይንቲሁ አበው
ሐና ዘወለደቶ ሳሙኤል ሰቆቃው ።

### ት ር ጉ ም

ሲቃዮች/ መንገዶችን መሄድ የወደደ ገብረ መርአዊ
ስንቅ /አለመታወቅን በሰሎሞን መስፈሪያ ወሰደ ፤
የመልኩ ውበት/ ብርሌ በደዌ (በህማም) ተሰብሯልና
ዳንኤል/ ልቡ



www.ethiopianorthodox.org

ለመታወክ/ አንበሳ የተሰጠ ሲሆን ።
የሀር ፈትል /ስጋውንም
ሌቦች /ትሎች በሚዛን ተካፈሏት ።
የልበኛ/ ትል ትእግስትም ከተገኘ ዘንድ
የዋሆች /ጣቶቹ በእንጨቶች አመለኩ ፤
ሀና የወለደችው ሳሙኤል ሰቆቃውም (ለቅሶም)
በአባቶች/ አይኖች ዘንድ የተናቀ አይደለም ።

### ም ስ ጢ ር

ሊሄድ የተዘጋጀ ድሃ መንገደኛ ተበድሮ መስፈሪያ ሙሉ እህል ስንቁን ይዞ ይሄዳል ፤ እንዲሁም ገብረ ክርስቶስ የተባለው መናኝ ከአባቱ ቤት ምቾት ይልቅ ስለ ክርስቶስ መንግስት የስጋ መከራ መቀበልን ወደደ ።

ብርጭቆም በድንጋይ እንደሚሰበር የገብረ ክርስቶስ የወጣትነቱ መልክ ውበት በደዌ ስጋ (በስጋ ደዌ ) ተለወጠ ።

ነቢይ ዳንኤል በጉድጓድ ተጥሎ ለአንበሳ እንደተሰጠ የገብረ ክርስቶስም ልቡና በክርስቶስ ፍቅር በመነሳሳት ጨከነ ፡ ሌቦችም የልብስ ፈትልን ቀምተው እንደሚካፈሉት የደዌ ስጋ ትሎችም የገብረ ክርስቶስን ስጋ በሉት ።

የዋሆች ሰዎች በእንጨቶች እንዳመለኩ ትል ከተፈጠረ ዘንድ የገብረ ክርስቶስ ጣቶች እንደ እንጨቶች ደረቁ ተቆራረጡ ። መካና የኖረች ሀና የወለደችው ሳሙኤልም በእስራኤል ዘንድ የከበረ እንደ ሆነ የድንግል ማርያም እናት ሀና ያለቀሰችውን ልቅሶ የገብረ ክርስ ቶስ አይኖች አለቀሱ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

የሰሎሞንን መስፈሪያ ባለቅኔው የጠቀሱበት ምክንያትም ሰሎሞን በገዛ ቤተ መንግስቱ እንግዳ ሆኗል ስለሚባል ገብረ ክርስቶስ ከታመመ በሁዋላ በቤተ ሰቦቹ ዘንድ አለመታወቁን ለማነፃፀር ነው ።

ወኀምስ መንገለ ደይን እንዘ ይወስዱኒ አፅራርየ ፤
ወዝ ኵሉ ነገር እምይኩን ብየ
ከዊኖተ ማይ እምኀየሰኒ በማሕፀነ እም ወላዲትየ ።

ት ር ጉ ም

ከእኔ ጋር ካሉት ከአምስቱ
ስራዎች የተነሳ እፈራና እንቀጠቀጣለሁ ፤
አንደኛው ነፍሴ በሞት ስትወጣ ይሆናልና
ሁለተኛም ወደመቃብር ስጋየ ስትወርድ ይሆናልና
ሶስተኛም በአምላኬ ፊት
ስቆም ሰውነቶቼ ይንቀጠቀጣሉና ፥
አራተኛም የኩነኔ ፍርድን ጆሮዬ ስትሰማ ነውና
አምስተኛው ወደ መከራ ጠላቶቼ ሲወስዱኝ ነውና ፤
ይህም ሁሉ ነገር ከሚሆንብኝስ
በወለደችኝ እናቴ ማህፀን ውሃ መሆን በተሻለኝ ነበር ።

ም ስ ጢ ር

አንድ እንግዳ ሰው «ለአገሩ እንግዳ ፥ ለሰው ባዳ» ሆኖ የሀገሩን ልማድና ጠባይ ሲጠይቅ ፥ «በዚህ ብትሄድ ሽፍታ ይቀማሃል በዚያም ብትሄድ ሌባ ያስፈራሃል» ሲሉት ይሸበራል ።

እንዲሁም ህግንና ስርአትን ጠብቆ እንዲኖር የተፈጠረ ሰው ህጉን ጥሶ ፥ ትእዛዙን አፍርሶ ፥ እንደስድ አደግ መረን ሲሄድ ከኖረ እነዚህ ከአንድ እስከ አምስት የተገለጡት ነገሮች ከሞት በሁዋላ ያስጉታል ። ስለዚህ እነዚህን ተዘክሮ (አስታውሶ) ከሞት በፊት ስህተትን በግንዛቤ አርሞ ፥ በደልን በንስሃ አስተስርዮ (አቃልሎ) መቆየት ይገባዋል ። ይህ ካልሆነ ግን ለሰው ጥንቱን አለመፈጠር ይሻለው ነበር ማለት በቅኔው ተገልጧል ።



## 303 ሥላሴ

ዘዘወልዴ (አለቃ)

አርካ ኬቱ ሁንዱማ ጨብሴ
ሌንጫ ጎፍታኮ ኢጆሌ ሌንጫ ፤
አሁንም የእውነት ግሩም አንበሳ የአንበሳ ኮርማ የቢያ
በከንድህ ሰበርኸው የሁሉን ሶማያ ።
ዱጉማ ጎፍታኮ ዱጉማ አሲ መና ኬቲ ገበያ
ሀሬ ጉደቴ ፈርዳን ፋለያ
ማሎ ማሎ ጎፍታ ኪያ !
መና ፈርዳ ፋደቴ አሀያ ።

ት ር ጉ ም

አንበሳ የአንበሳ ልጅ
ጌታየ ! ክንድህ ሁሉን ሰበረች ፤
አሁንም የእውነት አስፈሪ አንበሳ የአገር የአንበሳ ኮርማ (አንተ)
የሁሉን በትር በክንድህ ሰበርኸው ።
እውነት ጌታዬ እውነት ከዚህ ገበያ/ ቤትህ
እንያ አይጠ መጎጥ ፈረሶች ሲናቁ አህያ ከፍ ከፍ ተደረገች ፤
ምነው ምነው የእኔ ጌታ !
የፈረስን ቤት አህያ ወሰደች ።

ም ስ ጢ ር

አንበሳ በጉልበቱ ሃይል ሁሉን እንደሚሰብር አፄ ምኒልክ ሁሉንም አልፈው ነገሱ ። ደግሞ ጡንቻው በጣም የጠነከረ ሰው ዘንጉን ሲሰብቀው እንደሚያነቅጨው ምኒልክ የባላባቶቹን ምኞት አከሸፉት ።



www.ethiopianorthodox.org

ከአህያም በማንኛውም ረገድ ፈረስ እንደሚበልጥ የታወቀ ሲሆን ፈረሱን ትቶ አህያይቱን ቀሚስ ማልበስ ወግ እንዳይደለ ፣ እንዲሁም ጨዋ ሳለ ሌላውን ማላቅ አይገባዎትም የማለት ምስጋናም ወቀሳም በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

## 304 መወድስ

ዘተክሉ (መምህር ፡ ዘዋሸራ)

ጉባኤ ዕፄያት ኮነት ሥጋ አካልከ ፤
እመ ዕፄያት ዘኢዮብ ሊቃውንተ ንጉሥ ኬንያ
ዛቲ ሥጋከ እስመ ይእቲ ኒቅያ
ወምድረ ኒቅያ አካልከ ነያ ፣
ተመትሮ ማዕበለ ደም
እንተ ኢፈርሀ ልብከ ገብረ መርዓዊ ኖትያ !
ቅርብትሂ ለተመትሮ ምድረ ቢታንያ
ኢየሩሳሌም እደ ዚአከ ማኅደረ ሕማም ሐዋርያ ፤
ወበበርእሶን ደመ እንዘ ይበክያ
ደናግለ ምትረት አጻብዒከ ገይሠ መቃብር አሌለያ ።

### ትርጉም

የአካልህ ስጋ የትሎች መሰብሰቢያ ሆነች ፤
የኢዮብ ትሎች የብልህ ንጉስ ሊቃውንት ቢሆኑ
ይህች ስጋህ ኒቅያ ናትና
አካልህም የኒቅያ ምድር ናትና ፣
መቆረጥ/ የደም ማእበልን
ልብህ ያልፈራ ዋናተኛ / ገብረ መርአዊ !
የህማም / ሀዋርያ ማደሪያ የሆነች ያንተ
እጅ ኢየሩሳሌም ለመቆረጥ / የቢታንያ ምድር ቅርብ ናት፤



በየራሳቸውም ደምን እያለቀሱ
የመቆረጥ ደናግል/ ጣቶችህ ወደ መቃብር ለመገስገስ
ማለዱ ።

### ምስጢር

ኒቅያ በ325 አ.ም. አርዮስን ለማውገዝ በሮሙ ንጉስ ቆስጠንጢኖስ ትእዛዝ ለተጠሩ ሊቃውንት (ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት) መሰብሰቢያ እንደሆነች የገብረ ክርስቶስ አካልም የስጋ ደዌ ትሎችን አፈራች ። ደግሞ የወንዝን ማእበል የዋናተኛ ልብ እንደማይፈራ የገብረ ክርስቶስም ልብ ደም ብቻ የሚያደርግ ደዌን አልተሰቀቀውም። ሀዋርያ የሰበከባት ኢየሩሳሌም ለቢታንያ ቅርብ እንደሆነች ህማሙ ያደረባት የገብረ ክርስቶስ እጅ ለመቆረጥ ሆነች ።

ሴቶችም (እነመግደላዊት ማርያም) እያለቀሱ ወደ ክርስቶስ መቃብር በማለዳ እንደሄዱ የገብረ መርአዊ ጣቶች በደም ጠልቀው ወደመቃብር ወረዱ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

## 305 መወድስ

ሚካኤል ሰዐር ምክረ አሕዛብ
እለ መከሩ ወኀብሩ በርስትከ ኢትዮጵያ ፤
ከመ ርስተ ባዕዳን ኮነት ርስተ ጴጥሮስ ሮምያ
ኢትኩን ለባዕዳን
ብሔረ አግዓዚ ሀገርከ ነያ ፣
እስመ ሰብአ ጽርእ ወአንጾኪያ
በልብሰ አባግዕ መጽኡ ወእንተ ውስጦሙ ሐራውያ ።
አራምሂ እንተ ኢጸግበ ምህርካ ጥቃሁ ሶርያ
ወኤፍሬም ለደዌሁ በመጽሔተ አካዝ እንተ ርእያ
በኢየሩሳሌም መከሩ ወተመነዩ ንዋያ ፤
እንዘ ርእሰ አራም ደማስቆ ወኤፍሬም ሰማርያ ።



www.ethiopianorthodox.org

## ት ር ጉ ም

ሚካኤል ! በርስትህ/ ኢትዮጵያ
ያበሩና የመከሩ የአህዛብን ምክር ሻር ፤
የጴጥሮስ ርስት/ ሮምያ የባእዶች ርስት እንደሆነች
አገርህ የሆነች
የእግአዝያን አገር ኢትዮጵያ ለባእዶች እንዳትሆን ፤
የፅርእና የአንፆኪያ ሰዎች
ውስጣቸው እሪያ ሲሆን በበጎች ልብስ (እንደ በግ ፀጉር
ለስልሰው) መጥተዋልና ።
የሶርያን ምርኮም ያልጠገበ አራምና
ደዌውን በአካዝ መስታወት ያየ ኤፍሬም
በኢየሩሳሌም መክረዋልና ገንዘቧንም ተመኝተዋልና ፤
የአራም ራስ ደማስቆ ሲሆንና ኤፍሬም ሰማርያ ሲሆን ።

## ም ስ ጢ ር

ጠላቶች ተሰብስበው በሌላው ላይ ሲመክሩ የሰማ ወዳጅ «እነእገሌን እወቅባቸው ፣ ውስጣቸው ርኩስ ሲሆን ቅዱስ መስለው መጥተዋል ። እገሌ ፣ እገሌና እገሌ በሞኝነት ተታለው በእገሌና በእገሌ ርስቶቻቸውን እንደተነቀሉ አንተም ይህችን መሳይ ርስትህን በእነዚህ አታላዮች ትነጠቃለህ» በማለት እንደ ሚያስጠነቅቀው ሁሉ ፤ ቅዱስ ሚካኤል ! ኢትዮጵያን በስጋዊውም በመንፈሳዊውም ከማይመስሏት ጠላቶችዋ ጠብቅልን ምክራቸውንም ለውጠው ይላሉ ባለቅኔው ።

ጴጥሮስ በሮምያ የመሰረተው ባህል በሌሎች ባህል እንደተለወጠ የኢትዮጵያ መንፈሳዊ ባህል በማይመስሏት ሰዎች ባህል እንዳይለወጥ አድርግልን ። በጉዳዩ ቸል እንዳትልም ይሄውና ! የፅርእና የአንፆኪያ ሰዎች ርኩስ ባህላቸውን በኢትዮጵያውያን ባህል ሸፍነው መጥተውልሃል ። በዚህም አይነት ተንኮል ከአሁን በፊት የአራምና የኤፍሬም ልጆች ኢየሩሳሌምን ለመውረር አቅደው ነበር በማለት ፀሎታዊና ጥቆማዊ ምስጢር በቅኔው ተመስጥሮበታል ።



## 306 መወድስ

ዘክፍለ ዮሐንስ (ዘጎንደር)

እምከዊነ ካህን ይኄይስ ከዊነ ኖላዊ ፣
ወጎለ እንስሳ ትትበደር እምቤተ መቅደስ ዐባይ ።
እስመ ቤተ መቅደስ ኮነት ቤተ ፈያታይ ፣
ወበላዕለ ኖሎት ኢሀለወ
በላዕለ ካህናት ዘሀሎ እከይ ፤
ትእምርተ ዝኒ ከመ ንርአይ
በጎለ እንስሳ ሠረቀ ዘኢየዐርብ ፀሐይ ፣
ወኖሎት ተዛውዑ ምስለ ሐራ ልዑል ሰማይ ።
ዓዲ እምቅድመ ዝንቱ እመካነ ኖሎት ወመራዕይ
ከመ ተጸውዑ ደምፀ እግረ ቃለ ዜና ሠናይ
ወልደ እንበረም ለምስፍና ወለቅብዐ መንግሥት ወልደ
ዕሤይ ።

## ት ር ጉ ም

ካህን ከመሆን እረኛ መሆን ይሻላል ፣
የእንስሶች በረትም ከታላቅ ቤተ መቅደስ ትመረጣለች።
ቤተ መቅደስ የሽፍታ ቤት ሆናለችና ፣
በካህናት ላይ ያለ
ክፋትም በእረኞች ላይ የለምና ፤
የዚህንም ምልክት እናይ ዘንድ
የማይጠልቅ (የማይጨልም) ፀሀይ በእንስሳ በረት ወጣ ፣
እረኞችም ከከፍተኛ ሰማይ ጌታ መላእክት ጋር አብረው
ተጫወቱ ።
ዳግመኛም ከዚህ በፊት ከእረኞችና ከመንጎች ቦታ
የእንበረም ልጅ (ሙሴ) ለመስፍንነት የእሴይም
ልጅ (ዳዊት) ለመንግስት ቅባት እንደተጠሩ የመል
ካም ወሬ ኮቴ ተሰማ ።



www.ethiopianorthodox.org

### ም ስ ጢ ር

«እናትና አባት ብዙ ይወልዳሉ፣ ሙያውንና ግብሩን አይተው አንዱን ይወዳሉ» እንዲሉ መወደድና መላቅ ከስራ መበጀት የተነሳ ነው ። እረኞች ከብቶቻቸውን ከማሰማራትና እርስ በርስ ከመጫወት በቀር ሌላ ተንኮል አለማሰባቸውን ለጊዜው በጨዋታም ቢጣሉ ወዲያውኑ መስማማታቸውን፣ ከቅንነታቸውም የተነሳ ክርስቶስ በእንስሶቻቸው በረት ሲወለድ እነርሱ ከመላክት ጋር ማመስገናቸውን በማመልከት ባለቅኔው ከካህንነት እረኝነት ከቤተ መቅደስ በረት ይሻላል ይላሉ ።

ደግሞ ክርስቶስ ስለቤተ መቅደስ ሲናገር «ቤቴስ የፀሎት ቤት ነበር! እናንተ ግን የቀማኞችና የሌቦች ቦታ አደረጋችሁት » እንዳለ እውነት ሊነገርባትና ሊሰራባት የተመሰረተችው ቤተ መቅደስ ማታለያና መቀሰጫ ስትሆን የከብቶች በረት ግን የክርስቶስ መወለጃና የመላእክት ማመስገኛ መሆኗን ገልጠዋል ።

ጥንቱንም ሙሴ ለመስፍንነት የእሴይ ልጅ ዳዊትም ለመንግስት የተመረጡት ከበጎችና ከእረኞች መካከል እንጂ ከቤተ መቅደስና ከካህናት መካከል አለመሆኑን ጠቅሰው ታላቁ ሊቅ ክፍለ ዮሀንስ በአስራ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረውን የካህናትን ማህበራዊ ግንኙነት በቅኔያቸው ምስጢር አስረድተዋል ።

## 307 መወድስ

ዘኀበዚ (አለቃ)

ቦ ሕስው ስመ ተጸውዖ፤
እስመ ቦ በባሕር ወላዲተ ማይ ዘትሰመይ
እንዘ ኢትወልድ ማየ ጸሊመ ባሕርይ፣
ወእንዘ አሐደ ኢይኴንን
ደከመ በጸዊረ ስም ማልኮስ ሀካይ፤



ወእንዘ በብርሃን ኢይትረአይ
ሀለወ ቄሣር በተሰምዮ ብሩህ ፀሐይ ።
ለድንግልሰ ትርጓሜ ስማ በበንባቡ ዕሩይ፤
ለእመ ፈለገ ንሰምያ አምጣነ ወልዳ ዕንቈ ባሕርይ፣
ወለእመ ንብላ ኵልነ ገራህተ ሠሉስ ዐባይ
ክርዳድ ዘኢሀለዎ ፍሬሃ ፍሬ ሥርናይ ።

### ት ር ጉ ም

የተዋሸ የተፀውኦ ስም አለ፤
ባህርዩ የጠቆረ ውሃን ሳትወልድ
የውሃ እናት የምትባል በባህር አለችና፣
አንድም ሳይገዛ
ስምን በመሸከም ሰነፍ ማልኮስ ደከሚልና፤
በብርሃንም ሳይታይ
ብሩህ ፀሀይን በመባል ቄሳር ኖሯልና ።
የድንግል ግን የስሟ ትርጓሜ በየንባቡ ትክክል ነው፤
ወንዝ ብንላት ልጅዋ እንቆ ባህርይ (የእንቁ እንቁ) ነውና
ሁላችን የታላቅ ማክሰኞ እርሻ ብንላትም
ፍሬዋ እንክርዳድ የሌለው የስንዴ ፍሬ ነውና ።

### ም ስ ጢ ር

ያለበቂ ሙያ የሚመሰገን ሰው መኖሩ የውሃ እናት በምትባለው በውሃ ውስጥ በምትኖር ተንቀሳቃሽ፣ የስሙ ትርጓሜ ንጉስ በሆነ በአይሁድ ሊቀ ካህናት በቀያፋ አገልጋይ በማልኮስና በሮም ንጉስ በቄሳር ስሞች የተረዳ ነው ። የቅድስት ማርያም የስሟ አጠራር ግን በተግባራዊ ምሳሌ የተመሰረተ መሆኑ በወንዝነቷ እንቁን ወለደች ። በእርሻነቷም የስንዴ ፍሬን አስገኘች ማለት በቅኔው ምስጢር ተገልጧል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ት ር ጉ ም

ገብረ ህይወት! የመላእክት
ዘመድ መባልህ ልክህ ነው ፡
ከምድር ፃድቃን ጋር ግን ዘመድን እንዳትሆን
የመብል ትውታን ( መብሏን መተው ) ባእድን አደረግህ ፡
በገድል ገዳም ውስጥ የከበደ የፍፁሞች ቀኖናን ይፈፅም
ዘንድ
እልፍ ጊዜ እልፍን ቢሰግድ
ለምድር መብል ያልተዋረደ ( ፃድቅ )
ከፃድቃን አንድ እንኳን አላገኘንምና ።

## ም ስ ጢ ር

አንድ ሰው ዝምድናውን ቆጥሮ የትውልድ አረጉን መዞ ለተወላጁ ሲያስረዳ ተወላጁ « ዝምድናችን እውነት ነው ፤ እንደ አንተ ዘርዝሮ ዝምድናችንን ያስረዳኝ የለም » ይለዋል ። በእንፃሩም ገብረ መንፈስ ቅዱስ በተፈጥሯቸው ሰው ሲሆኑ በግብራቸው እንደ መልአክ ሆኑ ፤ ከሰው ወገን ፃድቃንም ቢሆኑ በእህልና ውሃ ያልኖረ የለም ። እቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ግን በፅኑ ተጋድሎ ሲኖሩ የእህልና ውሃ ክጃሎት( ፍላጎት )ጠፍቶላቸው ፣ አምላካቸውን ማመስገንን ብቻ እንደ እህልና ውሃ ተመግበው ኖሩ ስለሚባል መልአክ መባል ይገባቸዋል ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## 312 ዘይእዜ

በንባብ ይትበወቅ ገጸ ሕሳዌ ፤
እሩመ እመ ይቤ እሰግድ ለሕፃነ ድንግል ሰጊደ
ሄሮድስ ጻድቀ አፍአ
በቀቲለ እሉ ሕፃናት ተግህደ ።
ወእመ ረበናት ገብሩ መጽሐፈ ሙሴ ዘኢፈቀደ



ፍትሐ ሞተ ብእሲት ቍር ለእመ ወረደ
በንሚሠ ዕፀው ዳንኤል ሐሰተ ረበናት አንደደ ።
ፍትሐ ሞተ ብእሲት ቍር ለእመ ወረደ

## ት ር ጉ ም

የውሸት ፊት በንግግር ይታወቃል ፤
ለድንግል ህፃን ስግደትን እሰግዳለሁ ቢል
የውጭ እውነተኛ ሄሮድስ
እነዚህን ህፃናት በመግደል ተገልጧልና ።
መምህሮችም የሙሴ መፅሀፍ ያልፈቀደውን ባደረጉ ጊዜ
የሴት ሞት ፍርድ / ብርድ ቢወርድ
ዳንኤል እንጨቶችን በመፈለግ የመምህሮችን እሰት
አነደደ ።
የሴት ሞት ፍርድ / ብርድ ቢወርድ

## ም ስ ጢ ር

« ተከናንቦ ቢተኙ ገልጦ የሚያይ አምላክ አለ » እንዲሉ አንድ የተከናነበ ሰው ክንንቡ ሲገለጥ ፊቱ እንደሚታይ ፣ የውሸታም ነገርም በእውነት መሳይ ቃል ቢሸፈን በፍፃሜው ይገለጣል። በመሆኑም አካል በልብስ እንደሚሸፈን ፣ «እሰግድለታለሁ » በማለት የማርያም ህፃን (ክርስቶስ ) ግድያን የደበቀ ሄሮድስ « አሳድጋቸዋለሁ » ብሎ የሰበሰባቸውን ህፃናት በመግደሉ ተንኮለኛነቱ ታወቀበት ።

እንዲሁም ብርድ በሆነ ጊዜ እንጨቶችን በእሳት አንድዶ እንደመሞቅ የዝሙት ስራቸውን በሶስና ሊፈፅሙ አስበው ባይሳካላቸው ፣ ከነውር የነፃችውን ሶስናን በነውረኛ ስም የሞት ፍርድ ያስፈረዱባት ረበናት (መምህራነ አይሁድ ) ተንኮል በዳንኤል ጥበብ ተከሰተ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።



www.ethiopianorthodox.org

## 313 መወድስ

ዘልሳነ ወርቅ (አለቃ)

አልቦ በምድር ምልእተ ፍጥረት
እንተ ኢይትዋረድ ሰብአ ክቡር በዘወለደ ፤
እንዘ ወልደ ንጉሥ ውእቱ ገብረ መርዓዊ ዘከሐደ
ክቡራነ አዝማዲሁ
በቤተ አቡሁ እስመ ኮነ ባዕደ ፥
ወድኅረ ዝንቱ አስተዋረደ
አባሁ ንጉሠ እንተ የዐቢ ፈድፋደ ።
ይትርፍሰ ነገረ ዝንቱ ከመ ተነግረ ገሃደ
በልደተ ዮሐንስ ወንጌላዊ ዘካርያስ ተዋረደ ፤
ወበልደቱ ለዮሴፍ አናግደ ጸዊር ክቡደ
ዘይትዌከፍ በሀገሩ ያዕቆብ ተአንገደ ።

### ት ር ጉ ም

ፍጥረትን በተመላች ምድር
የከበረ በወለደው የማይዋረድ ሰው የለም ፤
የከበሩ ዘመዶችን የካደ ገብረ ክርስቶስ
የንጉስ ልጅ ሲሆን
በአባቱ ቤት ባእድን ሆኗልና ፥
ከዚህ በሁዋላም እጅግ
የገነነ ንጉስ አባቱን አዋርዷልና ።
የዚህስ ነገር እንደተነገረ ይቅርና
በወንጌላዊ ዮሀንስ ልደት ዘካርያስ ተዋረደ ፤
በዮሴፍም መወለድ ከባድን የመሸከም እንግዶችን
በአገሩ የሚቀበል ያእቆብ እንግዳ ሆነ ።



### ም ስ ጢ ር

ገብረ ክርስቶስ በገዛ ፈቃዱ የንጉስ አባቱን ቤት ትቶ በመሄዱ መፃተኛ መሆኑንና ያእቆብ በችግር መሰደዱን ፥ ዘካርያስም በልጁ በዮሀንስ ምክንያት አንገቱን በሰይፍ መቆረጡን በማስረዳት በሰው ልጆች ላይ የሚሆነውን የማጣትንና የማግኘትን ፍርርቅ የሚያሳይ ምስጢር በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

## 314 መወድስ

ዘአካለ ወልድ (መምህር)

አኮ ቀሊል ለዘይጸውሮ
እብነ አድማስ ረኃብ እንተ ይሰብር ክሣደ ፥
ወከመ ኢቀሊል ለጾር አጠየቀነ ገሃደ
ኤልያስ ሐመልማለ ከርሡ በረኃብ ዘነደ ፤
አድባረ ብካይ አመ ያደ
እስመ በዐይኑ ነጸረ እንተ ብእሲት እደ ።
ረኃብሂ ሐፂነ ከርሥ እመ ኢኮነ ክቡደ
ለፈርዖን ጸላኢሁ በከተማ በትሩ እምኢሰገደ ፤
ወእምሀገሩ ከነዓን እምኢተሰደ
ያዕቆብ በሀገሩ ብዙኃ ዘለመደ ።

### ት ር ጉ ም

አንገትን የሚሰብር የአድማስ
ድንጋይ /ራብ ለሚሸከመው ቀላል አይደለም ፥
ሆዱ/ ቅጠል በራብ /እሳት የነደደ ኤልያስም
ለሸክም ቀላል እንዳይደለ በግልፅ አስረዳን ፤
የልቅሶ ተራራዎችን በዞረ ጊዜ
የሴትን እጅ በአይኑ አይቷልና ።
ራብ/ የሆድ ብረትም ከባድን ባይሆን ኖሮ



www.ethiopianorthodox.org

ቀይሕ ፈረስ ልብሰ ከለሜዳ
ወካልእ ልብስ ፈረሰ ታቦር ጸዐዳ
ቀይሕ ፈረስ ልብሰ ከለሜዳ ።

ት ር ጉ ም

ተመኪ ክርስቶስ በወይን ወንዝ
ግዮን የአባቱ/ይሁዳ ልብስን ካጠበ ብሁዋላ፣
አይነቱ እንግዳ በሆነ
በእናቱ ልብስ ፀሀይ በታቦር ልብስን አነጣ ፤
ቀይ ፈረስ / የከለሜዳ ልብስና ሌላ ነጭ የታቦር ፈረስ/
ልብስም
የፍዳ መጨረሻ በሆነ በችግሩ ወራት
የባህርዩን ብልፅግና (ክብሩን) አሳየ ።
የፍዳ መጨረሻ በሆነ በችግሩ ወራት

ም ስ ጢ ር

ልብስ አጣቢ ልጅ በወንዝ ውሃ አጥቦ ያነጣውን ያባቱን ልብሰ በፀሀይ እንደሚያደርቅ ክርስቶስ ከይሁዳ ወገን (ከማርያም) ሰብአዊ ባህርያን ባህርይ አድርጎ በነሳው (በወሰደው) ስጋ በደብረ ታቦር የመለኮቱን ባህርይ ገለጠበት ። የሀብታም ሰው ብልፅግናም በፈረሱና በበቅሎው እንደሚታወቅ ክርስቶስም «በሰውነቱ ቀይ በመለኮቱ ነጭ » መባሉ ትህትናውንና ክብሩን ይገልጣሉ በማለት ባለቅኔው የክርስቶስን አምላክነት በቅኔያቸው ምስጢር ያስረዳሉ ።

## 320 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ይቤ ዮሐንስ መምህረ ብዙኃን ውሉድ
አክብሮ ሰንበት ሰይፍ በአንብሮ እግር ወእድ ።



ት ር ጉ ም

ብዙ የሆኑ ልጆች መምህር ዮሀንስ
ሰይፍ/ ሰንበትን ማክበር እጅንና እግርን በማሳረፍ ነው
አለ ።

ም ስ ጢ ር

የልጆች መምህር ሲመክር « ሰንበትን ማክበር እጅንና እግርን በማሳረፍ ነው » ይላል ፤ እንዲሁም ክርስቶስን ያጠመቀ ዮሀንስ አንገቱን በሰይፍ ሲቆረጥ ራሱ በክንፍ ወደላይ ወጣ ፤ ከአንገቱ በታች ያለ አካሉ እጆቹና እግሮቹ በመሬት ወደቁ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## 321 ሥላሴ

ዘካማ ( ቁሰገበዝ )

ሱርስተ ወዕብራይስጠ
ኢትትናገር ላእክ ልብሰ ባሕታዊ
መኑ ከልአከ ለነቢበ ሰብዓ በፍቅድ
እስመ አንተ ሥርግወ ዘሙሴ ወአሮን ኤፉድ ።
ቶማስሰ መምህር ዘንብሎ እምነ አእላፍ ውሉድ
በከናፍሪሁ ጽጌ በረድ
ነበበ የውጣ በማእከለ ዐውድ ፤
ወዳግመ ተርጎማ ለዮድ ።

ት ር ጉ ም

የባህታዊ ልብስ መልእክተኛ
ሰባን (ቋንቋ) በቁጥር ለመናገር
ሱርስትና እብራይስጥን እንዳትናገር ማን ከለከለህ ?

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

የሙሴንና የአሮንን የክህነት ልብስ የተሸለምህ ነህና ።
ከአእላፍ (ከብዙዎች) ምርጥ የምንለው መምህር ቶማስ ግን
የበረዶ አበባ በሆኑ ክንፈሮቹ
የውጣን በአደባባይ መካከል ተናገረ ፤
ዮድንም ዳግመኛ ተረጎማት ።

ም ስ ጢ ር

ከጌታ ልብስን የተሸለመ መልእክተኛ ሸላሚውን አመስግኖ ሲወጣ የቅርብ ጓደኛው የቀረ ነገር እያስታወሰ «ለምን እንደዚሁ ሳትል ቀረህ» ይለዋል ። እንዲሁም የተክለ ሃይማኖት ልብስ እን ደለባሹ ፃድቅ ከአመሰገነ ዘንድ ፣ ከሆነ አይቀር ሰባ ሁለት ቋን ቋን እንደሀዋርያት ሊናገር በቻለ ነበር ። የእነአሮን ልብስም የሚ ንሿሿ ድምፅ ያለው ሻሁራ ያለበት እንደነበረ የተክለ ሃይማኖት ልብስ ቅዱስ ቅዱስ . . . የሚል ድምፅ አሰማ ይላሉ ባለቅኔው ።

ደግሞ አንድ መምህር እያነበበ እንደሚተረጉም ቶማስ የውጣ ንና ዮድን አነበበና ተረጎመ ማለት ፣ የግሪክ ፊደል የውጣ ቅፅ ልና እዝል የሌለባት ወጥ እንደሆነችና የእብራይስጥ ፊደል ዮድም አንድ ወጥ እንደ ሆነች እርሱም ህዋሳቱን ሁሉ በከሀዲዎች ሰይፍ ተቆርጦ ምልምል ግንዱን ቀረ ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## 322 መወድስ

አልቦ ዘመድ ጊዜ ተዋርዶ
ወይከውን ባዕደ ጊዜ ተዋርዶ ዘመድ ፤
እመሰ ይትሌዐል በንብረተ ሥጋ ማዕድ
ጥቀ ዘመድ ወጥቀ ነገድ
ባዕድ ይዘመድ
እምነበ አልቦ ነገድ ወእምነበ አልቦ ትውልድ ።
ሶበሂ ተሰአልዎ ለሐዋርያ አይሁድ



ኅደገ ፈጣሪሁ ወቆመ ምስለ ባዕድ ፤
ዘመድሰ ዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ
እስመ ኢተፈልጠ ምስለ እሙ እስከ መቃብረ ይወርድ ።

ት ር ጉ ም

በመዋረድ ጊዜ ዘመድ የለም ፣
ዘመድም በመዋረድ ጊዜ ባእድን ይሆናል ፤
የስጋ ንብረት በሆነ ማእድ ከፍ ባለ ጊዜ ግን
እንኳን ዘመድ ፣ እንኳን ወገንና
ነገድ ከሌለበትና
ትውልድ ከሌለበት መጥቶ ባእድ ይዘመዳል ።
አይሁድም ሀዋርያን (ጴጥሮስን) በጠየቁት ጊዜ
ፈጣሪውን ተወና ከባእድ ጋር ቆመ ፤
ዘመድስ ዮሀንስ ወልደ ነጎድጓድ ነው
ወደ መቃብር እስኪወርድ ድረስ ከእናቱ ጋር አልተለ የምና ።

ም ስ ጢ ር

ሾላ በአፈራ ጊዜ ወፎች በቅርንጫፎቹ ፣ ህፃናትም በስሩ እንደሚሰበሰቡ ሁሉ አንድ ሰው ሀብት ባገኘና በተሾመ ጊዜ ዘመዱ ባእዱ አፋሽ አጎንባሹ ሁሉ ያገለግለዋል ፤ እጅብ እጅብ ያደርገዋል። በተሻረና በደኸየ ጊዜ ግን እንኳን ባእዱ ዘመዱ ይርቀዋል ። እንደዚ ሁም ሁሉ ክርስቶስ አርብ ሊሰቀል ሀሙስ ማታ ተይዞ ሳለ ፣ ተማ ሪው ጴጥሮስ « ኢየሱስን ታውቀዋለህን ?» ተብሎ ቢጠየቅ አላ ውቀውም ብሎ መምህሩን ካደና ከአይሁድ ሰዎች ጋር እሳቱን ይሞቅ ጀመር ።

አንዳንድ መንፈሰ ጠንካራ ወዳጅ ግን በማግኘቱና በደ ስታው ጊዜ የተጠጋውን ወዳጁን በችግሩና በመከራውም ጊዜ አይለ የውም ። ዮሀንስ ወልደ ነጎድጓድም ቀድሞ በባለሟልነት በክርስቶስ አጠገብ እንደተቀመጠ በመስቀልም ስር ሳይለየው ዋለ የክርስቶስንም እናቱን በአደራ ቃል ተቀበለ ማለት በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

www.ethiopianorthodox.org

ሀይወት በአባትና በልጅ ልማድ አልተጨነቀም ። እንደ ይስሀቅም ጊዜ ለልጁ ቤዛ በግን ከልጁ መስቀል ስር አላስገኘም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።

## 334 ግእዝ ጉባኤ ቃና

ዘካሣ ( ቁስ ገበዝ )

ምዕመናን ለቅብዕ ብእሴ ነቢብ አእላፈ
ሎቱ እርምሙ ወኢተሀብዎ አፈ ።

ት ር ጉ ም

አማኞች ! ብዙ ለሚናገር ሰው/ ቅቤ
ዝም በሉለት አፍም አትስጡት ።

ም ስ ጢ ር

ነገረኛን ሰው የሚያሸንፈው ዝምታ እንጂ ብዙ መናገር አይደለም ። በአንፃሩም አማኞች ለቅቤ አፍ አትስጡት በማለት በፆም ጊዜ አፋችሁ ቅቤ አይቅመስ ብለው ባለቅኔው ፆመኞችን በቅኔያቸው ምስጢር አስጠንቅቀዋል ።

## 335 ዘይእዜ

ዘለማ ኀይሉ ( አለቃ )

ነጸረ ጴጥሮስ ዖፈ ሰማይ
እንበለ ማእረር ወዘርዕ ለአሠንዮ ጽርሕ ትሩፍ ፤
እስመ እንበለ ዘርዕ ወማእረር
ለምጽላለ ርእሳ ዘትጻሙ ዖፍ ።
ወእመ ይሰምዕ ቃለ እምነ ደመና ልብሰ መትከፍ



www.ethiopianorthodox.org

ተዘከረ ታቦር በዓለ መጽሐፍ
ድንጋፄ ለጴጥሮስ ከመ ደዌሁ ዘዘልፍ ።
ተዘከረ ታቦር በዓለ መጽሐፍ

ት ር ጉ ም

ጴጥሮስ ያለዘርና አዝመራ
ትርፍ ቤትን ለማሳመር የሰማይ ወፍን ተመለከተ ፤
ወፍ ያለዘርና አዝመራ
ለራሷ ማረፊያ የምትጥር ናትና ።
ከትከሻ ልብስ/ ደመና ቃልን በሰማ ጊዜም
ባለ መፅሀፍ/ ታቦር አስታወሰ
ድንጋጤ የጴጥሮስ የዘወትር በሽታው እንደሆነ ።
ባለመፅሀፍ/ ታቦር አስታወሰ

ም ስ ጢ ር

ክርስቶስ «ወፎች ሳይዘሩና ሳይማርሩ እንዲመገቡ ተመልከቱ» ያለውን ጴጥሮስ በደብረ ታቦር አፀደቀ ፤ ምክንያቱም ወፎች ያለ ዘርና ያለአዝመራ እንደሚመገቡ ፣ እርሱም ለቤት ስራ የሚያስፈልጉት ነገሮች ሳይኖሩ «ሶስት ቤቶችን ሰርተን በዚህ ብንኖር መልካም ነው» ብሏልና ። በዚህም ላይ የደመና ነጎድጓድን ሰምቶ የደነገጠ መፅሀፍን መርማሪ ሰው ድንጋጤ በሽታ እንደሆነ ያስታውሳል ፤ እንዲሁም የወልድ ልብስ እንደበረዶ በሆነበት (በነጣበት) በደብረ ታቦር ጴጥሮስን ድንጋጤ እንደ በሽታ እንዳስተኛው ነተገረ ማለት ጭምር በቅኔው ተመስጥሮበታል ።

## 336 መወድስ

አ አብዳን ሰብአ ገላትያ
ዘገፋዕናክሙ ምንት ሰብአ ደብረ ምጥማቅ አእላፍ ?
ንቃወ ምዝባሬ ካልእ ዘጥቅመ ሰናዖር ዖፍ
ለቤተ መቅደስነ ትንግርዋ

የክረምቱ ማእበል በወሰዳቸው እቃና ሰው ላይ ደለል ሲደልልባቸው (ሲጭንባቸው) የጮሁ ሰዎችን ሰምቶ ችግራቸውን የሚረዳላቸው አይገኝም ። እንዲሁም በኦሪትም በወንጌልም መማለጃን መቀበበልና ፍርድን ማጣመም እንዳይኖር ቢነገርም ትእዛዙን የሚጠብቀው አልተገኘም ፤ ድሃውን ሃብታም በገንዘብ ተዳለለበት ። ዳኞችም ምስክሮችም በገንዘብ እየተደለሉ አዳፍኔ ሆኑ ። ማእበሉም ከወንዙ ድንጋግ (ወሰን) አልፎ እንደሚጎርፍ እብለት በዛ ።

ዘንጋዳ የሚባለው ያገዳ እህል አበባውን ፡ አርግፎ ለጋ ፍሬ ሲደመድም ጭቅጭቅ ጨቅጭቃል ይባላል ። ቃሉ ከወቀሳ ነገር ጋር ይሞካሻል ። በዚህ አተረጓጎም ግን ለጋ ፍሬን ያዘ ነፍስ አዋለ ማለት ነው ። ይሁን እንጂ በወርቁ በኩል የሙግትን ነገር ይዟል። ዘንጋዳ ሲባልም በሰም በኩል የአገዳ እህል ሲሆን ፡ በወርቁ በኩል ዘንጋ ፡ ዳ ፡ እንደማለት ሁለት ቃላት ይሆንና የቸልታን ፍች ይሰጣል ። ሰነፍ ምርት ማለትም በሰም በኩል ከደቃቁ ገለባው ጨርሶ ያልጠራው ፊስ (ርጋፊ) ሲሆን በወርቅ በኩል የሰነፍ ሰው ስራ ይሆናል።

በመነጠፍ ማለት ደሞ በሰም በኩል ከአፈር ጋር መቀላቀል ሲሆን በወርቅ በኩል የተረሳው መዝገብ ከመዛግብት ውስጥ መቀበሩን ያወሳል ። የዘንጋዳው ፍሬ ጨርሶ ከረገፈ ራሱ ቆረቆንዳ ይሆንና በማጭድ እንደፍሬያማው ሳይቆረጥ እንደሚቀር በሌሎቹ መዛግብት ውስጥ የተቀበረው የድሃው ሰው ጉዳይ በጭቅጭቅና በሙግት እንዳለ ሳይወሰን ቀረ ። «ወፍ ጠባቂ ለወፍ ጠባቂነት ቢቀጠር ፡ ድንጋይ ለቃሚ (አቀባይ) ቀጠረ» እንዲሉ ወፍ ጠባቂው ጠጠር አቀባዩን ሲያዝዝ የጠጠሩ ቅጥረኛ ጠጠሩን እስኪያቀብለው ወፉ የዘንጋዳውን ፍሬ ያወልበዋል (ይጨርሰዋል) ። ከመዝገብ ቤት ሰራተኛ ራስ ላይ የማይወርድ አሜትም የበላዮችን (የባላስልጣኖችን) ቁጣ ሲያመጣና አንዱ በሌላው ሲያመካኝ የመንግስት አደራ አልተጠበቀም ማለት በቅኔው ተመስጥሯል ።



# የባለቅኔዎች አጫጭር የህይወት ታሪክ

(የሚቀጥሉት የባለ ቅኔ ሊቃውንት አጫጭር ታሪኮች ባብዛኛው ከ«መፅሀፈ ቅኔ ፡ ዝክረ ሊቃውንት» እንዲሁም ከ«የቀድሞ ቅኔዎች ከነትርጓሜአቸው» የተቀሰሙ ናቸው ። ሰፋ ያለውን ታሪክ ከእነዚሁ መፃህፍት መመልከት ይቻላል ።)

## ሀይለ ስላሴ (መልአከ ሀይል)

መልአከ ሀይል ሀይለ ስላሴ ወልደ ሀና በሸዋ ክ/ ሀገር በደብረ ብርሃን ስላሴ በ1870 እ.ም. ተወለዱ ። በሸዋ በወሎና በጎጃም አድባራትና ገዳማት ከነበሩ ሊቃውንት ዜማ ፡ ቅኔና የመፃህፍት ትርጓሜ ተምረዋል ።

መልአከ ሀይል ሀይለ ስላሴ ትምህርታቸውን ጨርሰው ከተመለሱ በሁዋላም በአዲስ አበባ ከተማ እንጦጦ ራጉኤልን በድብትርና አገልግለዋል ። ብሉያትም በተተረጎሙ ጊዜ ከሌሎች ሊቃውንት ጋር ሆነው ሲራክንና ሰሎሞንን ተርጉመዋል ። ከዚህም ጋር አንደኛ የመካነ ህይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስን ደብር በአለቅነት ሁለተኛ እንጦጦ ራጉኤልን መልአከ ሀይል ሆነው አስተዳድረዋል ። መንፈሳዊ ጉባኤም ሲቋቋም በአባልነትና በመንፈሳዊ ዳኝነት አገልግለዋል ።

መልአከ ሀይል ሀይለ ስላሴ በተወለዱ በ85 አመታቸው በ1955 አርፈው በመካነ ህይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

## ሀይሌ ጉልቤ (አጋፋሪ)

አጋፋሪ ሀይሌ ጉልቤ የሸዋ ክፍለ ሀገር ተወላጅ ናቸው ። አዲስ አበባ በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ስላሴ መጀመሪያ በደብተርነት ሁዋላም አጋፋሪ ተብለው አገልግለዋል ። በቅኔ ሙያቸው የተመሰገኑ ነበሩ ።

## ለማ ሀይሉ (አለቃ)

አለቃ ለማ ሀይሉ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት መጨረሻ በመቄት (ላስታ) በአገረ ገነት ኪዳነ ምህረት አጥቢያ ተወለዱ ። አለቃ ለማ በላስታ ፥ በጎንደር በጎጃምና በሸዋ እየተዘዋወሩ ዜማ ቅኔና መፃህፍት ትርጓሜ አጥንተዋል ።

አለቃ ለማ በ1883 ኢ.ም. የአዲስ አበባ መንበረ ፀባኦት ቅድስ ስላሴ የሀዲስ መምህር ሆነው ተሾመዋል ። ከ1906 ኢ.ም. ጀምሮ በሀረር በአደሬ ጢቆ መካነ ስላሴ ደብር የሀዲስና የሃይማኖተ አበውን ትርጓሜ እያስተማሩ አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። ከዚህም ሌላ በአዲስ አበባ የቀጨኔ መድሃኔ አለምና በሀረር የጢቆ መካነ ስላሴ አድባራትን በአለቅነት አስተዳድረዋል ።

አለቃ ለማ የመፅሀፈ ቄርሎስን አንድምታ ትርጓሜና የሀዲስ ኪዳንን ነጠላ ትርጓሜ አዘጋጅተዋል ። ለቅዱሳት መፃህፍት ትርጉም ስራም ከተመደቡት ሊቃውንት አንዱ በመሆን ሃይማኖተ አበውን ተርጉመዋል ።

አለቃ ለማ በተወለዱ በ99 አመታቸው በአዲስ አበባ ከተማ ጥር 14 ቀን በ1959 ኢ.ም. ከዚህ አለም ተለዩ ።



## መርሻ ሀይሉ (መጋቢ ፡ ዘዲማ ጊዮርጊስ)

መጋቢ መርሻ ሀይሉ በጎጃም ክ/ ሀገር በታላቁ ገዳም ዲማ ጊዮርጊስ በ1840 ኢ.ም. ተወለዱ ። ፀዋትወ ዜማ (የዜማ አይነቶችን) ና የመፃህፍት ትርጓሜን በዚያው በገዳሙ ከሚገኙት ሊቃውንት ተምረዋል ። ቅኔም አለቃ ተክለ ጽዮን ዲማ በነበሩበት ዘመን ከርሳቸው ተምረው በቅኔ አዋቂነት የተመሰገኑ ሆነዋል ።

እኚህ ሊቅ የዲማ ጊዮርጊስ መጋቢ ሆነው አገልግለዋል ። በ1888 ኢ.ም. ለጉዳይ አዲስ አበባ እንደመጡ በድንገት ታመው ስላረፉ በአራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

## መርአዊ (አለቃ)

አለቃ መርአዊ በወሎ ክፍለ ሀገር ግሸን ደብረ ከርቤ ተወልደዋል ። የቁም ዜማ ፥ ያቋቋምና የቅኔ ባለሙያ ነበሩ ። በንጉስ ሚካኤል ጊዜ የተንታ ሚካኤል ደብተራ ሆነው አገልግለዋል ። በተለያየ ጊዜም የደሴ ተክለ ሃይማኖት ደብርና የመቅደላ ቤተ ክርስቲያን አለቃ ሆነው ሰርተዋል ።

## መኮንን ስሎሞን (አለቃ)

አለቃ መኮንን ስሎሞን ከአቶ ስሎሞን ግፋ ወሰንና ከወ/ሮ ማብረጃ መንገሻ ሸዋ በደብረ ሊባኖስ አካባቢ በ1871 ተወልደዋል ። በተወለዱበት ቀበሌ ንባብና ቅኔ ተምረዋል ። ከዚህ በሁዋላ ቦሩ ሜዳ ስላሴ ሄደው ከመምህር ወልደ ሚካኤል ሀዲስና ሊቅ አጥንተዋል ።

አለቃ መኮንን ሰለሞን በደብረ ሊባኖስ ገዳም ትርጓሜ መፃህፍት እያስተማሩ ኖረዋል ። በዚህም ጊዜ ገድለ ተክለ ሃይማኖትን

www.ethiopianorthodox.org

ድርሳነ ማህየዊንና ስአታትን ተርጉመው በግእዝና በአማርኛ አሳትመዋል።በተጨማሪም መፅሀፈ ሀዊን ከግእዝ ወደ አማርርኛ ተርጉመዋል።

አለቃ መኮንን ስሎሞን የአራተማርያምን አለቅነት ተሾመው መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን ሳያቋርጡ አርፈው በደብረ ሊባኖስ ገዳም ተቀብረዋል ።

## ስመኝ (መሪጌታ)

መሪጌታ ስመኝ በጎጃም ክፍለ ሀገር በእርባብ ወረዳ ጠለዛሞ ማርያም ተወለዱ ። በጎጃም አድባራትና ገዳማት ከነበሩ መምህራን ፀዋትወ ዜማና ቅኔ ተምረዋል ። የተመሰገኑ ቅኔ አዋቂ ነበሩ። እኒህ ምሁር በጠለዛሞ ማርያም ደብር ተቀምጠው ለረጅም አመታት ድጓ ያስተምሩ ነበር ። ከጉባኤያቸውም ብዙ ደቀ መዛሙርት ተምረው ለመምህርነት በቅተዋል ። ድጓ ሲያስተምሩም ዜማውን ብቻ ሳይሆን የንባቡንም ከየት መጣ ጭምር ይነግሩ ነበር ይባላል።

## ቀስሙ (መምህር)

መምህር ቀስሙ በጎጃም ክ/ ሀገር በዋሸራ ማርያም ተወለዱ ። በዚያው በትውልድ አገራቸው ተምረው መሀፅፈ መነኮሳትና ቅኔ ሲያስተምሩ ኖረዋል ። ከጉባኤያቸውም ብዙ ሊቃውንትን በትምህርት ወልደዋል ። ጉባኤያቸውን ሳይፈቱ የዋሸራን ገዳም በመምህርነት ሲያስተዳድሩ ኖረው በሞት ተለይተዋል ።

## በዛብህ ወንድም (አለቃ)

አለቃ በዛብህ ወንድም በጎንደር ክ/ሀገር እስቴ ወረዳ በመካነ ኢየሱስ አካባቢ በ1870 አ.ም. ግድም ተወልደዋል ። በመካነ ኢየሱስ ደብር ሀዲስ ካጠኑ በሁዋላ ድባና ቅዱስ ሚካኤል ሄደው



ከመምህር ወልደ ሚካኤል ፍትሀ ነገስት ተምረዋል ። ወደ ሸዋ መጥተው ከአለቃ ወልደ ጊዮርጊስ መፅሀፈ ሊቃውንት ቀፅለዋል ።

አለቃ በዛብህ ወንድም በጎንደር ክ/ሀገር ሊቀ ካህናትና የደብረ ታቦር መድሀኔ አለም አለቃ ሆነዋል ። ከዚያም በሁዋላ ወደአዲስ አበባ መጥተው የማህደረ ስብሀት ልደታ አለቃ ሆነው ርስትም ቦታም ተቀብለዋል ። በቦታቸው ላይ የመድሀኔ አለምን ቤተ ክርስቲያን አሰርተው ንብረታቸውን አውርሰው ሲኖሩ ሰኔ 28 ቀን በ1956 አ.ም. አረፉ ።

## ተክለ ሃይማኖት (አቤቶ)

አቤቶ ተክለ ሃይማኖት በጎንደር በበየዳ ኢየሱስ ደብር በ1635 አ.ም. ተወለዱ ። የአቤቶ ተክለ ሃይማኖት አባት እንድርያስ የአፄ ሱስንዮስ ዘመድ ነበር ይባላል ።

አቤቶ ተክለ ሃይማኖት የአራቱን ጉባኤ የባህረ ሀሳብና የቅኔ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ ጉባኤ ዘርግተው ሲያስተምሩ ኖረዋል ።

## ተክለ ፅዮን (አለቃ)

አለቃ ተክለ ፅዮን በሸዋ ክ/ሀገር በአንኮበር ወረዳ ሀር አምባ በሚባል ቀበሌ በ1820 አ.ም. ተወለዱ ። በአንኮበር ከተማ ከአለቃ ወልደ ስላሴ ትርጓሜ መፃህፍት ተምረዋል ። ወደ ጎጃም ተሻግረው ሞጣ ጊዮርጊስ በተባለው በስመ ጥሩው ደብር ከአራት አይናጎሹ የብሉያትን ትርጓሜ አጥንተዋል ። ብሉይና ቅኔ አዋቂ ነበሩ ።

አለቃ ተክለ ፅዮን በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ብሉይና ቅኔ ማስተማር ጀመሩ ። ከዚያም ወደሸዋ ተመልሰው በአንኮበር ከተማ የማስተማር ስራቸውን ቀጥለዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

በ1870 እ.ም. ግንቦት 21 ቀን በወሎ ክፍለ ሀገር ቦሩ ሜዳ ስላሴ በአፄ ዮሀንስ ዘመን ከተደረገው የሃይማኖት ክርክር በሁዋላ አለቃ ተክለ ፅዮን ወደኢየሩሳሌም ተሰደው ሄደው ህዳር 29 ቀን በ1881 እ.ም. አርፈው ከዚያው ተቀብረዋል ።

## ተክሌ (መምህር ፡ ዘዋሸራ)

መምህር ተክሌ በጎጃም ክ/ሀገር ዋሸራ ማርያም ተወልደዋል ። ዜማ ፡ ቅኔና መፃህፍት ትርጓሜ ተምረዋል ። በጣም የተመሰገኑ የቅኔ መምህር ነበሩ ። በዚህም ምክንያት ከዜማና ከመፃህፍት ትርጓሜ ሙያቸው ይልቅ የቅኔ ትምህርት ጉባኤያቸው ሰፍቶ ብዙ ሊቃውንትን አውጥተዋል ። እስከሞቱም ድረስ ከጉባኤ አልተለዩም ። መምህር ተክሌ በ98 አመታቸው አርፈው በሀገራቸው ዋሸራ ማርያም ተቀብረዋል ።

## ተገኝ (መልአከ ፀሀይ)

መልአከ ፀሀይ ተገኝ በጎጃም ክፍለ ሀገር በብቸና አውራጃ በደባይ ጥላትግን ወረዳ ወንዳሳ ቁስቋም ተወለዱ።ከአለቃ ሽፉ ወልደ ጊዮርጊስ ተምረዋል ። ቅኔና መፅሀፍ አዋቂና ተመራማሪ ሊቅ ነበሩ ።

መልአከ ፀሀይ ተገኝ ደብረ ማርቆስ ሲተከልና ሲደበር ጀምሮ ሊቀ ጠበብት ሆነው አቅንተዋል ። የቤተ ክርስቲያኑን ፕላንም ራሳቸው አውጥተው አናጢዎቹን እየመሩ አሰርተዋል ይባላል ።

መልአከ ፀሐይ ተገኝ በምርምርና ፈጠራ ስራቸው 1ኛ/ በኢትዮጵያ የሚገኙ መፃህፍትን ዝርዝርና የሚገኙበትንም ቦታ የሚያመለክት ፡ 2ኛ/ በኢትዮጵያ የነበሩ ሊቃውንትና ደጋግ ሰዎችን የህይወት ታሪክ ፡ 3ኛ/ የሊቃውንቱን ቅኔ ፡ 4ኛ/ የኢትዮጵያን ታሪክና የሰንደቅ አላማን ክብር የሚያስረዱ መፃህፍትንና ሌላም ብዙ አይነት ፅሁፍ አዘጋጅተው ነበረ ይባላል ።



www.ethiopianorthodox.org

እኒህ ሊቅ ከ1929 እስከ 1930 እ.ም. ባለው ጊዜ አርፈው በዚያው ደከመው ባቀኑት በደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

## ንጉሴ ይመር (አለቃ)

አለቃ ንጉሴ ይመር በጎጃም ክፍለ ሀገር ዲማ ጊዮርጊስ ተወለዱ ። በዚያው በትውልድ ቦታቸው ዜማ ከመሪጌታ ደርሰህ ፡ቅኔ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስ ፡ መፅሀፍም ከመምህር እንግዳ እሸት ተምረዋል ። የሰአሊነት ሙያ ስለነበራቸው አለቃ ንጉሴ በጎንደር ክፍለ ሀገር ኮስተት ዮሀንስ ፡ አጋጥ ፅዮን ፡ ጓሳጥ ሀናና ሽምላኮ ጊዮርጊስ የሚባሉ አብያተ ክርስቲያንን ስለዋል ። ወደሸዋም መጥተው ደንዲ የምትባልለዋን ደብር ተሾመው ገበዝም አለቃም እየሆኑ አስተዳድረዋል ። በወሎ ክ/ሀገር በደሴ ከተማ የዳኝነት ስራ ሰርተዋል ። ከፋሽስት ወረራም በሁዋላ አጋምና ጊዮርጊስን አለቅነት ተሾመዋል ።

አለቃ ንጉሴ በትምህርት ሚኒስቴር ባስተማሪነት ተመድበው ሲሰሩ ቆይተው በ1948 እ.ም. አርፈው በደጀን ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

## አካለ ወልድ (መምህር)

መምህር አካለ ወልድ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተወልደው ጎንደር ከመምህር ሀሊብ ተምረዋል ። በወሎ ክፍለ ሀገር በሚገኘው ቦሩ ሜዳ ስላሴ ገዳም ተቀምጠው አራቱን ጉባኤያት ያስተምሩ ነበር ። በቅኔም እጅግ የተመሰገኑ ሊቅ ናቸው ። ከሊቅነታቸው የተነሳ አፄ ቴዎድሮስ መምህር አካለ ወልድን «ይዋጓል እንደ ገብርዬ ይማሯል እንደ አካልዬ» ብለው አመስግነዋቸዋል ይባላል ። እኒህ ሊቅ ከአፄ ቴዎድሮስ እስከ ንግስት ዘውዲቱ ዘመን ከጉባኤ ሳይለዩ ኖረው ህዳር 29 ቀን በበ1912 እ.ም. አርፈው ባስተማሩበት ገዳም ቦሩ ሜዳ ስላሴ ተቀብረዋል ።

## አድማሱ ጀንበሬ (መልአከ ብርሃን)

መልአከ ብርሃን አድማሱ በጎጃም ክፍለ ሀገር በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ነሀሴ 1 ቀን በ1985 አ.ም. ተወለዱ ።

መልአከ ብርሃን አድማሱ በጎጃም ከአለቃ ገብረ ኤልያስና ከአለቃ ገብረ ማርያም ብሉይና ቅኔ ፤ በሸዋ ከካቢው መምህር ወልደ ስላሴ ብሉይ ፡ በወሎ ከደሴው መልአከ ገነት አፈወርቅና ከቦሩ ሜዳ ስላሴው ሊቅ ከመምህር አካለ ወልድ ሀዲሳትንና መፃፍተ ሊቃውንትን አጥንተው በዲማ ጊዮርጊሰ ገዳም መፅሀፍና ቅኔ አስተምረዋል ።

መልአከ ብርሃን አድማሱ የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ትምህርት ቤት መጋቤ ምስጢር ፡ የብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ጠበብትና መልአከ ብርሃን ፡ በቤተ ክህነትም የመንፈሳዊ ጉባኤ መማክርት አባል ፡ የታሪክና የድርሰት ክፍል ሀላፊና የሊቃውንት ጉባኤ ሊቀ መንበር ሆነው አገልግለዋል ።

መልአከ ብርሃን 1ኛ ኮኩሀ ሃይማኖት ፡ 2ኛ መድሎተ አሚን፡ 3ኛ መፅሀፈ ቅኔ ዝክረ ሊቃውንት ፤ 4ኛ የበገና መዝሙር የተባሉ መፃህፍትን አዘጋጅተው አሳትመዋል ።

እኒህ ሊቅ በአዲስ አበባ ከተማ ሀምሌ 24 ቀን በ1962 አ.ም. በሞት ተለዩ ።

## አድማሱ ጌትዬ (ንቡረ እድ)

ንቡረ እድ አድማሱ ጌትዬ በሸዋ ክፍለ ሀገር ሀር አምባ በሚባል ስፍራ ተወለዱ ። በዚሁ በተወለዱበት ክፍለ ሀገር ተምረው የተመሰገኑ ሊቅ ሆነዋል ።

በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የካህናት ባልደረባ ሆነው ሰርተዋል ። ከዚያም በሁዋላ ንቡረ እድ አድማሱ መልአከ ገነት ተብለው



አራዳ ጊዮርጊስን አለቅነት ተሾመዋል ። ንቡረ እድም ሆነው አዲስ አለም ማርያምን ሲያስተዳድሩ ሰኔ 9 ቀን በ1921 አ.ም. አርፈዋል ።

## አፈወርቅ ዘውዴ (አለቃ)

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ በወሎ ክፍለ ሀገር በአማራ ሳይንትና ቦረና አውራጃ መጋቢት 15 ቀን በ1909 አ.ም. ተወለዱ ።

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ በወሎ ፡ በጎጃምና በጎንደር አድባራትና ገዳማት ከነበሩ ሊቃውንት ዜማ ቅኔና የመፃህፍት ትርጓሜ አጥንተዋል ።

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ የቅኔ መምህርነት ሙያቸውን ካደላደሉ በሁዋላ በጎጃም ፡ በወሎና በአዲስ አበባ 36 አመታት አስተምረው ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። በተጨማሪም በወሎ የደብረ ከርቤ ጊዮርጊስ አለቃ ሆነው 22 አመታት አገልግለዋል ።

አለቃ አፈወርቅ ዘውዴ ለግእዝ መማሪያ የሚሆኑ መፃህፍትን በሰባት ደረጃ መድበው አዘጋጅተዋል ። የመጀመሪያው መፅሀፍ «ፀያሒ ፍኖት» በሚል ርእስ በ1958 አ.ም. ታትሟል ።

እኒህ አረጋዊ አባት የግእዝ ቅኔ ሊቅ አሁንም በመንበረ መንግስት ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እያስተማሩ በኮንትራት ተቀጥረው በኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዴሚ በግእዝ ቅኔና መፃህፍት አንድምታ ትርጓሜ ክፍል ቅኔያትን በመተርጎም ፡ በማመስጠርና በመተረክ ይሰራሉ ። ቅኔዎቻቸውም በቁጥር 187 ፡ 241 ፡ 263 እና 337 ይገኛሉ ።

## እንግዳሸት (መምህር)

መምህር እንግዳሸት በጎጃም ክፍለ ሀገር ዲማ ጊዮርጊስ ተወለዱ ። በዚያው በተወለዱበት ገዳም ተምረው የሀዲስ የሊቅና የቅኔ መምህር ለመሆን በቅተዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

መምህር እንግዳሸት በቅኔ ሙያቸው እጅግ የተመሰገኑ ከመሆናቸውም በላይ የቅኔ ዘረፋና ነጠቃ ስጦታ እንደነበራቸው ይነገራል ። ቅኔም ሆነ የመፃህፍት ትርጓሜ በሚያስተምሩ ጊዜ ለደቀ መዝሙሮቻቸው ምስጢሩን አብራርተው ያስተምሩ ነበር ይባላል ።

መምህር እንግዳሸት የዲማ ጊዮርጊስን ገዳም መጀመሪያ በግብዝና ቀጥሎም በመምህርነት ሲያስተዳድሩ ኖረው ጥቅምት 25 በ1923 አ.ም. አርፈዋል ።

## እንግዳ ደስታ (አለቃ)

አለቃ እንግዳ ደስታ በጎንደር ከተማ በአፄ ቴዎድሮስ ዘመነ መንግስት ተወለዱ ። ንባብና ዜማ በጎንደር ከተማ ከተማሩ በዋሁላ ወደ ጎጃም ሄደው በዲማ ጊዮርጊስ ቅኔ ከመምህር ተጠምቆ ተማሩ ። ቁም ፅህፈትና ቅኔ አዋቂ ነበሩ ። አለቃ እንግዳ ደርቡሽ ጎንደርን በወረረ ጊዜ ወደእንግሊዝ አገር ሄደው እንግሊዝኛ ተምረው አስተርጓሚ ሆነዋል ።

አለቃ እንግዳ ደስታ እንግዳ ዳንኤል ተብለው ይጠሩ ነበር ። በእንግሊዝ አገር 24 አመት ከኖሩ በሁዋላ ወዳገራቸው ተመልሰው በጎንደር ክፍለ ሀገር መጀመሪያ ፋሲለደስን በሁዋላ አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤልን በአለቅነት አስተዳድረዋል ።

አለቃ እንግዳ በ1914 አ.ም. በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተቀጥረው መፃህፍትን ከእንግሊዝኛ ወደአማርኛ ከአማርኛ ወደ እንግሊዝኛ በመተርጎም ሲያገለግሉ ኖረው በ1934 አ.ም. አርፈዋል ።

## እንግዳ ወርቅ ሀይሉ (አለቃ)

አለቃ እንግዳ ወርቅ ሀይሉ በጎንደር ከተማ በዘመነ መሳፍንት ተወለዱ ። በተወለዱበት ከተማ ተምረው የሀዲስና የቅኔ ባለሙያ ለመሆን ችለዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

አለቃ እንግዳ ወርቅ ሀይሉ መጀመሪያ ጎንደር ኤዎስጣቴዎስን ፣ ሁዋላም ጎንደር መድሀኔ አለምን አለቅነት ተሾመው ሲያገለግሉ በ1906 አ.ም. ሀምሌ 12 ቀን አርፈዋል ።

## ከብቴ (አቃቤ ሰአት)

አቃቤ ሰአት ከብቴ የታወቁት የጎንደር ሊቃውንት የመምህር ኤስድሮስና የመምህር መልከ ጼዴቅ ደቀ መዝሙር ነበሩ ። የአራቱ ጉባኤ (ብሉይ ፣ ሀዲስ ፣ መጽሀፈ ሊቃውንትና መፅሀፈ መነኮሳት)ና የአቡሻህር ሊቅ ናቸው ። ከዚህም ጋር በፀዋትወ ዜማና በቅኔ እውቀታቸው እጅግ ተመስግነውበታል ።

እኒህ ሊቅ በጎንደር ከተማ በደብረ ምጥማቅና በግምጃ ቤት ማርያም ተቀምጠው እያስተማሩ አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። የታወቁት ሊቅ አለቃ ወልደ አብም የእርሳቸው ደቀ መዝሙር እንደሆኑ ይነገራል ። በተጨማሪም እኒህ ሊቅ አቃቤ ሰአት (ሰአት ጠባቂ በዚህ ጊዜ ውጡ ፣ በዚህ ጊዜ ግቡ የሚል የአፄ ዳኛ) ሆነው አገልግለዋል ። የአቃቤ ሰአት ከብቴ የመምህርነትና የሹመት ዘመን ከመናኔ መንግስት ተክለ ሃይማኖት እስከ ፈፃሚ መንግስት ተክለ ጊዮርጊስ ዘመነ መንግስት ነበር ይባላል ።

## ካሳ (ቄስ ገበዝ)

ቄስ ገበዝ ካሳ በጎጃም ክ/ሀገር በይልማናና በዴንሳ አውራጃ በጎንጅ ቴዎድሮስ ደብር ተወልደዋል ። በዚሁ በተወለዱበት ደብር ከነበሩ ሊቃውንት ተምረው የተመሰገኑ የብሉይና የቅኔ መምህር ሆነው ተመርቀዋል ።

ቄስ ገበዝ ካሳ ከአፄ ዮሀንስ እስከ ንግስት ዘውዲቱ ዘመነ መንግስት የጎንጅ ቴዎድሮስ የብሉያትና የቅኔ መምህር ሆነው አያሌ ደቀ መዛሙርትን አስተምረው በመምህርነት መርቀዋል ።

በተጨማሪም የደብሩ ቄሰ ገበዝ ሆነው አገልግለዋል ። ቄሰ ገበዝ ካሳ ከቅኔያቸው ክብደት የተነሳ እቡይ የሚባል ቅፅል እንደተሰጣቸው ይተረካል ።

## ክፍለ ዮሀንስ

ታላቁ ሊቅ ክፍለ ዮሀንስ መጀመሪያ በጎጃም ክፍለ ሀገር በመተከል አውራጃ ውስጥ በሚገኘው በጋሾላ ገዳም ተምረዋል ። ቀጥሎም በጎንደር ከተማ አራቱን ጉባኤ ፡ ቅኔና ዜማ አጥንተዋል ።

ክፍለ ዮሀንስ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ አራቱን ጉባኤና ቅኔ እያስተማሩ በተማሩበት ከተማ በጎንደር ደብረ ብርሃን ስላሴ ብዙ ዘመን ኖረዋል ። እኒህ ሊቅ ብዙ ሊቃውንትን በትምህርት ወልደዋል ። የመምህርነት ዘመናቸውም ከአድያም ሰገድ ኢያሱ እስከ አፄ በካፋ ዘመነ መንግስት መጨረሻ እንደነበር ይተረካል ። ክፍለ ዮሀንስ በቅኔያቸው እጅግ ከተመሰገኑት ሊቃውንት አንዱ ናቸው ።

## ወልደ ማርያም ሀብቴ (አለቃ)

አለቃ ወልደ ማርያም ሀብቴ በሸዋ ክፍለ ሀገር በደብረ ሲና አውራጃ በሾተል አምባ በእታ ሰኔ 21 ቀን በ1879 እ.ም. ተወልደዋል።

በሸዋ በወሎና በጎንደር ክፍላተ ሀገር ከነበሩ መምህራን ፀዋትወ ዜማና ቅኔ ተምረው የዝማሬ መዋስእትና የአቋቋም መምህር ለመሆን በቅተዋል ።

አለቃ ወልደ ማርያም ሀብቴ በሸዋ ክፍለ ሀገር በመናገሻ ማርቆስ ተቀምጠው ዝማሬ ፣ መዋስእትና አቋቋም እየነገሩ በግብዝናና በልቅና ደብሩን ሰላሳ አንድ አመት አስተዳድረዋል ።



## ወልደ ዮሀንስ (መልአከ ብርሃን)

መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሀንስ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተወለዱ ። በጎጃም ክፍለ ሀገር በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ከአለቃ ተክለ ፅዮን ቅኔ ከመምህር ገብረ ህይወት የመፃህፍት ትርጓሜ ተማሩ ። ወደሸዋም ተመልሰው ከአለቃ ገብረ ኢየሱስ የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ አጥንተዋል ።

መልአከ ብርሃን ወልደ ዮሀንስ የመፃህፍትን ትርጓሜ አስተምረው አያሌ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። ከደቀ መዛሙርታቸውም መካከል ሊቁ ገብረ ክርስቶስ አንዱ ናቸው ። በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት ፍትሀ ነገስት አውጭ ሆነው አገልግለዋል ።

## ወልደ ገብርኤል (ራስ)

ራስ ወልደ ገብርኤል በትግራይ ክፍለ ሀገር በአጋሜ አውራጃ የተወለዱ የደጃች ሰባጋዲስ ልጅ ናቸው ። በራስ ስኡል ሚካኤል ቤት አድገዋል ። በዚሁ ጊዜ ቅኔ ከነአግባቡና የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ተምረዋል ። ራስ ወልደ ገብርኤል የተመሰገኑ ቅኔ አዋቂ ነበሩ ።

## ወልደ ጊዮርጊስ (አለቃ)

አለቃ ወልደ ጊዮርጊስ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተወለዱ ። በጎንደርና በጎጃም አድባራት ከነበሩ ሊቃውንት ተምረዋል ። በንጉስ ተክለ ሃይማኖት ዘመን በጎጃም ክፍለ ሀገር የገወራ ቁስቋምን በአለቅነት እያስተዳደሩ የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ ያስተምሩ ነበር ። በብዙዎች በጎጃም አድባራት ሪም ተተክለው ስማቸው ሸዬ ወልደ ጊዮርጊስ እየተባለ ተፅፏል ።



www.ethiopianorthodox.org

እኒህ ሊቅ በጎጃም ክ ሀገር በደብረ መዊእ ገዳም ለረጅም አመታት ቅኔ ከነአገባቡ በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን አፍርተዋል ። ከቀደ መዛሙርታቸውም አንዱ አለቃ ቃለ ማእነቅ የመናገሻ ማርያም የቅኔ መምህር ናቸው ።

ሊቀ ህሩያን ዘገየ ገብረ ስላሴ ለብዙ ዘመናት በትጋትና በቅንነት ሲያስተምሩ ኖረው በ1932 ኢ.ም. አርፈዋል ። (ታሪኩ የልጅ ልጃቸው መሪጌታ በላይ መኮንን ካቀረቡት በምህፃር የቀረበ ነው።)

## ዠማነህ (ደብተራ)

ደብተራ ዠማነህ በሸዋ ክፍለ ሀገር ተወልደዋል ። በአዲስ አበባ ከተማ አራዳ ጊዮርጊስ ሲተከል ጀምሮ በደብተርነት ሲያገግሉ ኖረዋል ። ደብተራ ዠማነህ ጥሩ ቅኔ አዋቂ ነበሩ ።

## ይትባረክ ቂርቆስ (መሪጌታ)

መሪጌታ ይትባረክ ቂርቆስ በጎጃም ክፍለ ሀገር በብቸና አውራጃ በደብረ ፅሙና ተወልደዋል ። በተወለዱበት በደብረ ፅሙናና በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ተምረው በድጓና በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል። ከዚህም ሌላ መርሀ እውር ፣ ቀመረ አረብ (ባህረ ሀሳብ) አዋቂ ነበሩ ። እኒህ ሊቅ መሪጌታ ያሬድ ቂርቆስም እየተባለ ይጠራሉ

መሪጌታ ይትባረክ ቂርቆስ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ ጎጃም በደብረ ፅሙና በወይባ ደብርና በእነብሴ ፣ ወሎ በአማራ ሳይንት ፣ ሸዋ በአራተ ማርያም ደብር ቅኔ አስተምረዋል ። ከዚያም በሁዋላ እንደገና ወደ ተወለዱበት ደብረ ፅሙና ተመልሰው በማስተማር ላይ እንዳሉ በ1946 ኢ.ም. አርፈዋል ።



## ደለለ (መሪጌታ)

መሪጌታ ደለለ በጎጃም ክፍለ ሀገር ዋሸራ ማርያም ተወለዱ ። ከስመ ጥሩው መምህር ተክሌ ዘዋሸራ ቅኔ ከነአገባቡና ከነእርባ ቅምሩ ተምረዋል ። የመምህራቸውን ወንበር ተረክበው ሲያስተምሩ አያሌ ደቀ መዛሙርትን አውጥተዋል ። መሪጌታ ደለለ ፍሬያማ የሆነ የማስተማር ስራቸውን በማከናወን ላይ አርፈው ተምረው ባስተማሩበት ዋሸራ ማርያም ተቀብረዋል ።

## ደመረ (ግራጌታ)

ግራ ጌታ ደመረ ትውልዳቸው በሸዋ ክፍለ ሀገር ነው ። በአዲስ አበባ ከተማ በአራዳ ጊዮርጊስ ደብር ቅኔ ሲያስተምሩ ኖረው አርፈዋል ።

## ደስ፦ታ (አለቃ)

ጋይንቴ ደስታ ትውልዳቸው በጎንደር ክፍለ ሀገር ጋይንት ነው ። የብሉይና የቅኔ መምህር ነበሩ ። ይህንኑ ሙያቸውን እያስተማሩ በሀረር ከተማ ይኖሩ እንደነበር ይነገራል ። ጋይንቴ ደስታ በቅኔ ሙያቸው እጅግ የተመሰገኑ ናቸው ።

## ድንቄ (አለቃ)

አለቃ ድንቄ በሸዋ ክ/ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ በጅሩና ወግዳ ወረዳ ሶምሳ በሚባል ቦታ ተወለዱ ።

የንባብ ትምህርትና መዝሙረ ዳዊትን ከፈፀሙ በሁዋላ ተጉለት ሄደው ተጉለቴ ዜማ ፣ ቅኔ ሰላሌ ከአለቃ ዘዮሀንስ ፣ ሀዲስ ካሊቃ ሀሩይ ተምረዋል ። የብሉያቱንም ትርጓሜ ዘልቀውታል ።

www.ethiopianorthodox.org 

www.ethiopianorthodox.org

## ገብረ ሥላሴ ክንፉ (መምህር)

መምህር ገብረ ስላሴ ክንፉ ትውልዳቸው በወለጋ ክፍለ ሀገር ነው ። ቅኔና መፅሀፈ ሊቃውንት በጎጃም ክፍለ ሀገር በየገወራ ማርያም ደብር ከአለቃ ሽዬ ወልደ ጊዮርጊስ ፣ ብሉይና ቅኔ በደብረ ማርቆስ ከመምህር ሰረገላ ብርሃን ፣ አገባብና እርባ ቅምር በደብረ ገነት ኤልያስ ከሊቀ ጠበብት አይችሀ ፣ የመፃህፍተ ሊቃውንትን ትርጓሜ በደንበጫ ሚካኤል ከመልአከ ሰላም ገብረ ማርያም (ቡሬ ገብረ ማርያም) ተምረዋል ። በተጨማሪም የፀዋትወ ዜማና የሀዲስ መምህር ሆነው ተመርቀዋል ።

መምህር ገብረ ስላሴ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ እየተማሩ ባደጉበት በየገወራ ማርያም ደብር ሀዲስና ቅኔ ማስተማር ጀመሩ ። ከዚህም በሁዋላ በደብረ ገነት ኤልያስ ተቀምጠው ቅኔ ከነአገባቡ ፣ ብሉይ ሀዲስና ፍትሀ ነገስት እያስተማሩ ብዙ መምህራንን መርቀው ሸመዋል ።

መምህር ገብረ ስላሴ በቅኔያቸው ከሚደነቁት ሊቃውንት አንዱ ናቸው ። እኒህ ሊቅ ከማስተማርና ምስጢረ መፃህፍትን ከመመርመር ሳይለዩ በ1938 አ.ም. አርፈው በደብረ ገነት ኤልያስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

## ገብረ ስላሴ (ንቡረ እድ)

ንቡረ እድ ገብረ ስላሴ በሸዋ ክፍለ ሀገር በደብረ ብርሃን ከተማ በ1837 አ.ም. ተወልደዋል ። በአንኮበር ከተማ ዜማና ቅኔ እየተማሩ አድገዋል ።

ንቡረ እድ ገብረ ስላሴ ከ1860 አ.ም. ጀምሮ ፀሀፌ ትእዛዝ ሆነው ሰርተዋል ። በ1900 አ.ም. በኢትዮጵያ የመጀመሪያው የፅህፈት



ሚኒስቴር ሆነው ተሾመዋል ። እንጦጦ ራጉኤል ሲተከል ጀምሮ አስተዳዳሪ ሆነው አገልግለዋል ። በ1920 አ.ም. የአዲስ አለም ማርያም ንቡረ እድ ሆነዋል ።

ንቡረ እድ ገብረ ስላሴ ጠቃሚ የሆነ አገልግሎታቸውን ሲያበረክቱ ኖረው በ1905 አ.ም. ጥቅምት 27 ቀን አርፈው በደብረ ሀይል እንጦጦ ራጉኤል ተቀብረዋል ።

## ገብረ ዋህድ ህሼ (አለቃ)

አለቃ ገብረ ዋህድ ህሼ በትግራይ ክፍለ ሀገር በእንደርታ አውራጃ ገረአልታ ልዩ ስሙ አባ ሰላማ በተባለ ቦታ ተወለዱ ። ቅኔ ፣ ዜማና ትርጓሜ መፃህፍት አዋቂ ነበሩ ።

አለቃ ገብረ ዋህድ በቤተ ክህነት የሊቃውንት ጉባኤ አባል ሆነው ሲሰሩ ቆይተው ታህሳስ 4 ቀን በ1961 አ.ም. አርፈው በአዲስ አበባ በመካነ ህይወት ገብረ መንፈስ ቅዱስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

## ጎሹ አራት አይና

አራት አይና ጎሹ በጎጃም ክ/ ሀገር ተወለዱ ። በታወቀው ደብረ ሞጣ ጊዮርጊስ ተምረው የአራቱ ጉባኤ መምህር ሆነው ተመርቀዋል ። አራቱን ጉባኤ ያጠናቀቁ ሊቅ በመሆናቸው «አራት አይና» የሚል ቅፅል ተሰጥቷቸዋል ።

አራት አይና ጎሹ በተማሩበት ደብረ ጉባኤ ዘርግተው አለቅነቱንም ደርበው የታወቁ ሊቃውንት እነመምህር ሰው አገኘሁን ፣ እነአለቃ ገብረ ኤልያስን ፣ እነመምህር ፀበሉን ፣ እነአለቃ ተክለ ፅዮንን ፣ እነአለቃ ስነ ጊዮርጊስን ፣ እነ መምህር ክፍለ ጊዮርጊስንና ሌሎችንም ብዙ ሊቃውንት አስተምረው የብሉያት ትርጓሜ መምህር አድርገው መርቀዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

እራት አይና ጎሹ በዘመናቸው እጅግ የታወቁና የተመሰገኑ የትርጓሜ መፃህፍትና የቅኔ ሊቅ ነበሩ ። እኒህ ሊቅ ከሚወዱት ጉባኤ ሳይለዩ ጥር 29 ቀን በ1861 ዓ.ም. አርፈው የውሽ ሚካ ኤል በተባለው ደብር ተቀብረዋል ።

## ጥበቡ ገሜ (መምህር)

አለቃ ጥበቡ ገሜ በሸዋ ክፍለ ሀገር በሰላሌ አውራጃ በጎሀ ፅዮን ከተማ ሰኔ 10 ቀን በ1873 ዓ.ም ተወለዱ ።

ጎሀ ፅዮን ከነበሩት ከአባ ገብረ ማርያም ዘንድ እስከ ግብረ ዲቁና ያለውን ትምህርት ተምረዋል ። ከዚያም ወደ ጎጃም ተሻ ግረው በዲማ ጊዮርጊስ ገዳም ቅኔ ከነአገባቡ ከመምህር ወልደ ጊዮ ርጊስ ፣ የብሉይን ትርጓሜ ከመልአከ ገነት ክፍሌና ከመምህር ገብረ ኤልያስ በሞጣና በደብረ ማርቆስ አድባራት ተምረው በመምህርነት ተመርቀዋል ። በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ በየጁና በሰቆጣ ከነበሩ ሊቃውንት የቅኔና የመፃህፍት ትርጓሜ ትምህርት ሙያቸውን አደ ላድለዋል ።

አለቃ ጥበቡ ገሜ በወሎና በሸዋ በሚገኙ ገዳማትና አድባ ራት አያሌ አመታት አስተምረው ብዙ የቅኔ መምህራንን መር ቀው አውጥተዋል ።

እኒህ ሊቅ 37 ዓመታት ባስተማሩበት በሸዋ በሰላሌ አው ራጃ በሚገኘው በስሬ መድሃኔ አለም ደብር በተወለዱ በ91 አመታ ቸው አርፈው ሀምሌ 27 ቀን በ1964 አ.ም. ተቀብረዋል ። (ታሪኩ ለአ ርባ ቀን መታሰቢያቸው ከታተመው ፅሁፍ በምህፃር የቀረበ ነው ።)

## ፈንታ ገብርየ (መልአከ ብርሃን)

መልአከ ብርሃን ፈንታ ገብርየ በጎጃም ክፍለ ሀገር በጎዛምን ወረዳ ዝግባ እቦ ተወልደዋል ። አባትና እናታቸው በልጅነታቸው



ስለሞቱባቸው ከፊደል እስከዳዊት ድጋም ያለውን በንጉስ ተክለ ሃይማት ግቢ ተማሩ ። ከዚያም ዜማ ቤት ገብተው ፀዋትወ ዜማ ፣ ቅኔ ከመምህር ሰረገላ ብርሃን ፣ ብሉያቱን ከአለቃ ገብረ ኤልያስ ፣ ሊቃውንቱን ከአለቃ ወልደ ጊዮርጊስ አጠኑ ። ፅህፈት ፣ ድጉሰት ስእል መሳልና ሀረግ መንደፍም ይችሉ ነበር ።

መልአከ ብርሃን ፈንታ ገብርየ በአለቅነት አጋምና ጊዮርጊስን መልአከ ብርሃን ሆነው ብቸና ጊዮርጊስን አስተዳድረዋል ።

እኒህ ሊቅ ሚያዝያ 27 ቀን በ1935 አ.ም. አርፈው በደብረ ማርቆስ ቤተ ክርስቲያን ተቀብረዋል ።

## ፈንቴ (መሪጌታ)

መሪጌታ ፈንቴ ዋሴ ትውልዳቸው በጎጃም ክፍለ ሀገር በዋ ሸራ ማርያም ገዳም ነው ። ከታላቁ ሊቅ ከመምህር ተክሌ ዘዋሸራ የቅኔ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በሁዋላ ወደአቸፈር ሄደው ከመም ህር ገሰሰ የጎዳና ቅኔ እውቀታቸውን አደላድለዋል ።

መሪጌታ ፈንቴ ተወልደው በተማሩበት በዋሸራ ማርያም ገዳም አስተምረው ብዙ የቅኔ መምህራንን መርቀው ሾሙዋል ። እኒህ አረጋዊ ምሁር ከጉባኤ ሳይለዩ ለብዙ ዘመናት ከኖሩ በሁዋላ ሀምሌ 25 ቀን በ1955 አ.ም. በ71 አመታቸው አርፈው በዚያው በዋሸራ ማርያም ተቀብረዋል ።



www.ethiopianorthodox.org

# ባለቅኔዎቹ

## በፊደል ተራ

(የቅኔዎቻቸው ቁጥሮች ከስሞቻቸው ጋር ሰፍረዋል ። ከስማቸው በፊት የኮከብ ምልክት የተደረገባቸው የህይወት ታሪካቸው ባጭሩ ተፅፎላቸዋል ) ።

| ተ. ቁ. | ሙሉ ስም |
|---|---|
| *1 | ሀይለ ስላሴ (መልአከ ሀይል) ፡ 284 ፡ 216 |
| *2 | ሀይሉ ( አጋፋሪ) ፡ 139 |
| 3 | ሀይሉ ( ዘመቀሌ) ፡ 268 |
| 4 | ሀይሌ (አለቃ) ፡ 283 |
| 5 | ሀይመት (ወይዘሮ) ፡ 250 |
| 6 | ሀሩይ (አለቃ) ፡ 273 ፡ 299 |
| *7 | ለማ ሀይሉ (አለቃ) ፡ 73 ፡ 88 ፡ 128 ፡ 333 ፡ 335 |
| 8 | ልሳነ ወርቅ (አለቃ) ፡ 313 |
| *9 | መርሻ (መጋቢ ፡ ዘዲማ ጊዮርጊስ ) ፡ 79 ፡ 265 |
| *10 | መርአዊ (አለቃ ፡ ዘተንታ) ፡ 120 |
| 11 | መንግስቱ ( መሪጌታ ) ፡ 85 ፡ 87 ፡ 184 |
| *12 | መኮንን ሰሎሞን (አለቃ) ፡ 75 |
| 13 | ምስራቅ (አለቃ ፡ ዘኤልሻማ) ፡ 65 |
| 14 | ምትኩ እውር (ዘደብረ ወርቅ ) ፡ 181 |
| 15 | ምትኩ ( መጋቢ ) ፡ 108 |
| 16 | ምንደስይል (ደብተራ ) ፡ 143 ፡ 219 |
| 17 | ሲኖዳ (ፀሀፊ ትእዛዝ ፡ ዘጎንደር ) ፡ 249 |
| 18 | ሳህሌ ወልደ ተክሌ (አለቃ) ፡ 228 |
| *19 | ስመኝ ( መሪጌታ ፡ ዘጠላዘሞ) ፡ 37 ፡ 58 ፡ 60 |



ethiopianorthodox
www.ethiopianorthodox.org

| ተ. ቁ. | ሙሉ ስም |
|---|---|
| 74 | ይግዛው ( አለቃ ፡ ዘደብረ ወርቅ ) ፡ 164 |
| *75 | የፍታሄ ንጉሴ ( ቀኝ ጌታ ) ፡ 61 |
| *76 | ደለለ ( መሪጌታ ፡ ዘዋሸራ ) ፡ 271 |
| 77 | ደመረ ( ግራጌታ ፡ ዘገነተ ፅጌ ) ፡ 110 |
| 78 | ደስታ ( አለቃ ፡ ዘተድባበ ማርያም ) 23 ፡ 92 |
| 79 | ደስታ ( መምህር ፡ ዘዋሸራ ) ፡ 293 |
| *80 | ደስታ ( አለቃ ) ፡ 294 |
| 81 | ደቀ እስጢፋ ፡ 197 |
| 82 | ዳኜ ( አለቃ ፡ ዘራጉኤል ) ፡ 103 |
| *83 | ድንቄ ( አለቃ ) ፡ 285 |
| *84 | ድንቆ ማርቆስ ፡ 205 ፡ 308 ፡ 311 |
| 85 | ጀምበሬ ( መሪጌታ ) ፡ 41 |
| *86 | ገብረ መስቀል ( መምህር ) ፡ 22 |
| 87 | ገብረ መድህን ( መምህር ) ፡ 153 |
| *88 | ገብረ መድህን ( አለቃ ፡ ዘአሰቦት ) ፡ 27 ፡ 207 |
| 89 | ገብረ መድህን ( አለቃ ፡ ዘሌመን ሰላሌ ) ፡ 111 |
| *90 | ገብረ መድህን ( ግራጌታ ) ፡ 57 |
| 91 | ገብረ መድህን ( መምህር ፡ ዘማህደረ ማርያም ) ፡ 326 |
| 92 | ገብረ ሚካኤል እውር ( ዘሰላሌ ) ፡ 231 |
| 93 | ገብረ ማርያም ( ቄስ ገበዝ ) ፡ 248 |
| *94 | ገብረ ስላሴ ክንፉ ( መምህር ፡ ዘኤልያስ ) ፡ 70 ፡ 86 ፡ 105 ፡ 155 ፡ 163 ፡ 170 ፡ 281 |
| *95 | ገብረ ስላሴ ፡ ( ንቡረ እድ ) 195 |
| 96 | ገብረ ኢየሱስ ( መምህር ) ፡ 4 |
| *97 | ገብረ ዋህድ ህሼ ( አለቃ ) ፡ 142 |
| 98 | ገብረ ጊዮርጊስ ( መምህር ) ፡ 29 |
| 99 | ገብረ ፃድቅ ( መሪጌታ ፡ ዘፍቼ ጊዮርጊስ ) ፡ 24 |
| 100 | ገብሬ ( አለቃ ፡ ዘደብረ ሊባኖስ ) ፡ 315 |
| 101 | ንዝሙ ( ደብተራ ) ፡ 174 |



| ተ. ቁ. | ሙሉ ስም |
|---|---|
| 102 | ጌቴ ገሞራው ፡ 151 |
| *103 | ጎሹ አራት አይና ፡ 251 |
| 104 | ጎበዜ ( አለቃ ) ፡ 307 |
| 105 | ጥበቡ ( መሪጌታ ) ፡ 52 |
| *106 | ጥበቡ ገሜ ( መምህር ) ፡ 141 ፡ 147 |
| 107 | ጫልቲ ሀይሉ (አባ) ፡ 166 |
| *108 | ፈንታ ጉብርየ ( መልአከ ብርሃን ) ፡ 6 |
| 109 | ፈንታየ ( አለቃ ) ፡ 127 |
| *110 | ፈንቴ ( መሪጌታ ) ፡ 15 |

www.ethiopianorthodox.org

# ከዚህ መፅሀፍ ቅርብ ዝምድና ያላቸው መፃህፍት ዝርዝር

**መፅሀፈ ቅኔ ፣**

ከብላቴን ጌታ ሀሩይ ወልደ ስላሴ ፣ አዲስ አበባ 1918 ።

**መፅሀፈ ቅኔ ፣ ዝክረ ሊቃውንት**

ከመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ፣ አዲስ አበባ 1963 ።

**ንባብ ወትርጓሜ ዘቅኔያት ፣ እእግደ ምስጢራት ፣**

ከመምህር ይሄይስ ወርቄ ፣ አዲስ አበባ 1960 ።

**የቀድሞ ቅኔዎች ከነትርጓሜአቸው ፣**

ከአለቃ ይኩኖ አምላክ ገብረ ስላሴ ፣ አዲስ አበባ 1959 ።

**ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት ፣**

ከሊቀ ስልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ፣ አዲስ አበባ 1963 ።

**መፅሀፈ ትዝታ ዘአለቃ ለማ ፣**

ከመንግስቱ ለማ ፣ አዲስ አበባ 1959 ።

**መፅሀፈ ሰዋስው ፣**

ከአለቃ ታየ ፣ ምንኩሉ 1889 ።

ethiopianorthodox

www.ethiopianorthodox.org